# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርኀ ግብር**


በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን
በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ
ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የውጤት ተዛምዶ


በ

በላቸዉ ማንደፍሮ



ሐምሌ፣ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የውጤት ተዛምዶ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረምረቃ መርኀግብር

ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) መርኃግብር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በ

በላቸዉ ማንደፍሮ

ሐምሌ፣ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድኅረምረቃ መርኀግብር**

# በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የውጤት ተዛምዶ

በ

በላቸዉ ማንደፍሮ

2015 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት፤**

**አማካሪ፡-**

ስም፤__________________ ፊርማ ____________ ቀን____________

**ፈታኞች፡-**

ስም፤__________________ ፊርማ____________ ቀን____________

ስም፤__________________ ፊርማ____________ ቀን____________

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ቦታና ጊዜ ሳይመርጡ በአካልም ሆነ በስልክ በጥናቱ ዙሪያ ጥያቄዎችን እንድጠይቅ ላበረታቱኝ፣ የጥናቴን ረቂቅ አንብበው ገንቢ አስተያየት በመስጠትና በማቃናት እና ቅንነት በተሞላበት ሁኔታ በመቀበል ይህ ጥናት አሁን ባለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለጥናቱ አስፈላጊውን መረጃ በተገቢው እና ሥርዓት ባለው መልኩ ስለሰጡኝ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመጨረሻም አቶ አሻግሬ ግባቱ የተለያዩ ስሌቶችን በSPSS Version 26 በመስራት ስላገዙኝ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ምስጋና ........ i
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3 የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 4
1.4 የጥናቱ አላማዎች ........ 4
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7 የቁልፍ ቃልና ሀረጋት ዐውዳዊ ብያኔ ........ 5
ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ........ 7
2.1 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ........ 7
2.1.1 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምንነት ........ 7
2.1.2 የክፍል ተሳትፎ ጠቀሜታ ........ 9
2.1.3 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መከሰቻዎች ........ 10
2.1.4 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ደረጃ መለኪያ ........ 11
2.1.4.1 በውይይት የማስተማር ዘዴ የሚያሳዩት ተሳትፎ ........ 12
2.1.4.2 በክርክር ወቅት የሚኖር የተማሪዎች ተሳትፎ ........ 13
2.1.4.3 በድራማ ማስተማር ........ 13
2.1.4.4 በትንሽ ቡድን ማስተማር ዘዴ የሚኖራቸው ተሳትፎ ........ 13
2.1.4.5 በጥያቄና መልስ የሚኖራቸው ተሳትፎ ........ 14
2.1.4.6 አሳታፊ ባልሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎች ተሳትፎ ........ 14
2.2 የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ........ 15
2.3 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 16
ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ........ 19
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 19
3.2 የመረጃ ምንጮች ........ 19
3.3 ናሙናና የናሙና አመራረጥ ........ 19
3.3.1 የትምህርት ቤት እና የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 19

3.3.2 የተማሪዎችና የመምህር ናሙና አመራረጥ ............ 20
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ............ 20
3.4.1 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምልከታ ............ 20
3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ ............ 21
3.4.3 የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ............ 21
3.5 የመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች ............ 22
3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ ............ 23
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ............ 26
4.1 የመረጃ ትንተና ............ 26
4.1.1 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ ............ 26
4.1.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ 27
4.1.3 የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት የጾታ ልዩነት ............ 28
4.2 የውጤት ማብራሪያ ............ 30
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት ............ 33
5.1 ማጠቃለያ ............ 33
5.1 አስተያየት ............ 34
ዋቢ ጽሑፎች ............ 36
አባሪ 1፤ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ መጠይቅ ............ 40
አባሪ 2፤ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ የምልከታ ቅጽ ............ 43
አባሪ 3፤ የጥያቄ ማውጫ ሰንጠረዥ ............ 45
አባሪ 4፤ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ............ 47
አባሪ 5፡- ለተጠኚዎች የቀረበው ፈተና አስተማማኝነት ለመፈተሽ የተሰበሰበ መረጃ ............ 55
አባሪ 6፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚለካውን መጠይቅ አስተማማኝነት ለመፈተሽ የተሰበሰበ መረጃ ............ 57
አባሪ 7፤ የጥያቄዎች ከፍተኛና ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን መለየት ብቃትናየክብደት ደረጃ ............ 58
አባሪ 8፡- የአማርኛ ትምህርት ፈተናው በፍተሻ ጥናት (Pilot study) የአስተማማኝነት ስሌት ውጤት ............ 60
አባሪ 9፡- የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁ በፍተሻ ጥናት (Pilot study) የአስተማማኝነት ስሌት ውጤት ............ 63
አባሪ 10፡- በምልከታ ወቅት የተሰበሰበው ዝርዝር መረጃ ............ 65

ሰንጠረዥ 11፡- በዋናው ጥናት ወቅት የተሰበሰቡ አጠቃላይ መረጃዎች......................66

ሰንጠረዥ 12፡- የተለዋዋጮቹ የውጤት ስርጭት ወጥነት ፍተሻ በግድለትና በዝብጠት ዜድ ውጤቶች ........................................................................................................... 68

ሰንጠረዥ 13፡- የሴትና የወንድ ተማሪዎች የውጤት ስርጭት ወጥነት ፍተሻ በሻፒሮ-ዊልክ . 69

ሰንጠረዥ 14፡- የሴት ተማሪዎች የውጤት ስርጭት ወጥነት ፍተሻ በግድለትና በዝብጠት ዜድ ውጤቶች ........................................................................................................... 69

ሰንጠረዥ 15፡- በሁለቱ ተለዋዋጮች ውጤቶች ውስጥ የፍንግጥ ነጥቦች (Outliers) አለመኖር ፍተሻ በባለሳጥን ግራፎች (Boxplots) ......................................................................... 70

ሰንጠረዥ 16፡- በሴትና በወንድ ውጤቶች ውስጥ የፍንግጥ ነጥቦች (Outliers) አለመኖር ፍተሻ በባለሳጥን ግራፎች (Boxplots)................................................................................... 71

ሰንጠረዥ 17፡- ሁለቱ ተለዋዋጮች ያላቸው ቀጥተኛ ግንኙነት (Linearity) ፍተሻ በብትን ግራፍ (Scatterplot) ተሰርቶ ........................................................................................ 72

ሰንጠረዥ 18፧ የስህተት መጠን ስርጭት (Homoscedasticity) ፍተሻ በብትን ግራፍ.......... 72

## የሰንጠረዥ ማውጫ

**ሰንጠረዥ** **ገጽ**

ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ....26

ሰንጠረዥ 4.2፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን የመተንበይ ድርሻ፣ በቀላል ድህረት ........ 28

ሰንጠረዥ 4.3፤ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 29

ሰንጠረዥ 4.4፤ የአማርኛ ቋንቋ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ........ 29

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሩ 48 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ በአመቺ የንሞና ስልት የተመረጠ ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በጠቅላይ የንሞና ስልት በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ከ48 ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸውን ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስቧል፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ (የጽሑፍ መጠይቁና የአማርኛ ቋንቋ ፈተናው) መረጃ ለመሰብሰቢያነት ከማገልገላቸው በፊት በፍተሻ ጥናት (Pilot Study) መረጃዎች ተሰብስበው፣ መረጃዎች በክሮንባኽ አልፋ ተፈትሸው የተገኘው ውጤት ከ0.7 በላይ በመሆናቸው (አስተማማኝ በመሆናቸው) ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ ከዚያም ጥናቱ ይዟቸው የተነሳውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ የቀላል ድህረታዊ እና የነጻ ናሙና ቲቴስት ስሌቶች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ($r=.642$፣ $P<.01$፣ ባለሁለት ጫፍ) እንዳለ እና የተዛምዶ ደረጃውም ከፍተኛ እንደሆነ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ፍተሻው አሳይቷል፡፡ ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2 = .412$፣ $\beta = .642$፣ $F(1፣ 47) = 32.267$፣ $t = 5.680$፣ $p = .000$) አሳይቷል፡፡ የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት አለመኖሩን የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ትንታኔው ($t(46) = .776$, $p = 0.442$) ያሳዩ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ልዩነት ተፈትሾ የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ($t(46) = .301$, $p = .765$) አለመኖሩን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት መምህራን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ቢያበረክቱ፤ መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ተማሪዎችም እንዲሳተፉ በማነቃቃትና አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን በመከተል ተሳትፏቸውን እንዲጨምር ቢያደርጉ፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና የትምህርት ውጤት ካላቸው ከፍተኛ ዝምድና አንጻር ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸውን በማሳደግ ውጤታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች መማሪያ መጻሕፍትንና የመምህር መምሪያዎችን ሲያዘጋጁ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ምቹ የሆነና የሚያበረታታ እንዲሆን ትኩረት ቢያደርጉ እና በሁለቱም ጾታዎች ያለው የተሳትፎ ምጥጥን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ቢደረግ የሚሉ አስተያየቶች በአጥኚው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ትምህርት ሰዎች እዉቀት፣ ክህሎት፣ እሴት፣ ልማት የሚያገኙበት ሂደት ነዉ፡፡ ስለዚህ ለማንኛዉም ሀገርና ማህበረሰብ ጠቀሜታዉ አጅግ የላቀ ነዉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ትምህርት ለአንድ ሀገር እድገት፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት የሚያበረክተዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነዉ፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከሚገኙ ሀገራት መካከል ለሚታየዉ ሰፊ ልዩነት ዋናው ምክንያት ትምህርት ነዉ፡፡ በርካታ ምሁራን ትምህርት ለማህበራዊ እድገት አስፈላጊ መሆኑን ይስማሙበታል፡፡

ትምህርት መደበኛና ኢመደበኛ በሆኑ ዐውዶች ይተገበራል፡፡ Candlin & Mercer (2001) እንደገለፁት መደበኛው ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት፣ መማሪያ መጻሕፍት በወጉ ተዘጋጅተውለት፣ የተወሰነ ጊዜ ተመድቦለት፣ በእቅድና ስልታዊ በሆነ ዘዴ በሰለጠኑ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ነው፤ መደበኛ የቋንቋ ትምህርትም የዚህ አካል ነው፡፡ ኢመደበኛ ትምህርት ከክፍል ወይም ከትምህርት ቤት መርሀ ግብር ዉጪ የሚከናወን ነው፡፡ በመደበኛ የትምህርት መርሀግብር ደግሞ ዘመናዊና ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዳሉ Ahmed (2015) ያስረዳሉ፡፡ ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ በርካታ ክንውኖችን እንዲያከናውን የሚጠበቅበት፣ ተማሪዎቹ ደግሞ ፍዝ ተቀባይ የሚሆኑበትና መምህሩም የእውቀት ምንጭ ተደርጎ የሚወሰድበት ነው፡፡ በአንጻሩ በዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ መምህሩ ተማሪዎችን የማነነሳሳትና አቅጣጫ የማሳየት ተግባርን በመከወን ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ነው (Tudor, 1993 & Ahmed, 2015):: በዘመናዊው የማስተማሪያ ዘዴ ማዕቀፍ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የማስተማሪያ ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎቹን የትምህርቱ ማዕከል በማድረግ ትምህርቱን የሚመራበት ነው፡፡ የትምህርቱ ሂደትም ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ከገቡ ጀምሮ መምህራን የተማሪዎችን ለውጥ እስከ ሚገመግሙበት ያለውን ጊዜ ይይዛል (Tudor, 1993)፡፡ ይህም መምህሩ ብቻውን በበላይነት የሚመራው ሳይሆን ተማሪዎችንም የሚያሳትፍበት ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርትን የመማር ማስተማር ተግባር በአንድ ወገን ብቻ ሊከወን የሚችል ባለመሆኑ ትምህርቱ ውጤታማ የሚሆነው በመምህሩ ጥረት ብቻ ሳይሆን በተማሪዎችም ተሳታፊነት ነው፡፡ ስለሆነም የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና በቀላሉ ለማስረጽ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ወሳኝነት አለው፡፡ Reed & Bergemann (1995) እንደገለጹት የመምህራን የክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር በጣም አስፈላጊው የመማር ማስተማር ተግባር ተማሪዎችን በትምህርቱ ስራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተፋጠነና የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢነት አለው፡፡ በተለይም በአሁኑ ዘመን የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ የሚሰጠው ትኩረት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተማሪዎች ተሳትፎ በመማር

ማስተማሩ ሂደት የሚበረታታ ተግባር ነው (Tudor, 1993)፡፡ ለዚህም የመምህራን የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ውጤት አለው (Richards, 2001)፡፡ Borich (2004) የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ መምህራን በክፍል ውስጥ ለገለፃ የሚያጠፉትን ረዥም ጊዜ በመቀነስ ተማሪዎች ሊሳተፉበት የሚያስችላቸውን ሰፊ የመወያያ ጊዜ መስጠትና በተግባሩ እንዲሳተፉ በማድረግ የመማር ማስተማር ስራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

የቋንቋ መምህሩ ሚና በክፍል ዉስጥ የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ማመቻቸት ነዉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ድጋፍ  በሚፈልጉበት ሁኔታ ነፃ ሆነዉ እንዲቀርቡ፣ የሚያዉቁትን ነገር ቋንቋዉን ተጠቅመው በተለያዩ አዉዶች መግለጽ እንዲችሉና በአጠቃላይ ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ሁኔታን መፍጠር ነዉ፡፡ Borich (2004) እንደሚገልጹት በመማር ሂደት የተማሪዉ ተሳትፎ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ የትምህርት ተሳትፎ መገለጫውም ተማሪዎች ለተለየዩ የትምህርት ዓይነቶች ራሳቸዉን በመስጠት ምን ያህል ሰዓታትን እንደሚጠቀሙ የሚያሳይ ነዉ፡፡ የተማሪዎች ዉጤታማነት ወይም ስኬታማነት ደረጃ የሚያሳየዉ ተማሪዎች ጥያቄዎችንና የተለያዩ የትምህርት ስራዎችን የመረዳትና በትክክል መስራታቸውን ነው፡፡

የክፍል ዉስጥ ጥያቄዎች በስፋት በጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተማርያ ስልቶች ናቸው፡፡ Hamilton &  Bradyን (1991) ጠቅሰው Eggen & kauchak (2013) እንደሚያስረዱት በክፍል ዉስጥ በመምህራን ተደጋግመው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎች ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና አላቸው፡፡ በተመሳሳይ ኤርሚያስ (1996) በትምህርት ሰዓት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚኖራቸዉ ተሳትፎ ለውጤታቸዉ የሚኖረዉ አስተዋጾ ከክፍል ዉጪ በጥናት ስልት ከሚያሳልፉት ጊዜ እኩል ክብደት እንዳለው አስረድተዋል፡፡ እንደ አብዛኛዎቹ የትምህርት ተሃድሶ ንድፈ ሐሳቦች ጥሩ የማስተማር ሥራ ሁልጊዜ ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሳሳ፣  በክፍል  ውስጥም  እንዲሳተፉ  የሚያደርግና  የትምህርት ዉጤትንም  የሚያሳድግ ነው፡፡

በአንጻሩ የትምህርት  ተሳትፎ  ብቻ  ለውጤት  መሳካት  ምክንያት  አይደለም የሚሉ ተመራማሪዎችም አሉ፡፡ Marx & Marion (1977) ትምህርቱ  ህይወታዊና  አስደሳች እንዲሆን ተማሪው በመማር-ማስተማሩ ሂደት በክፍል ዉስጥ መሳተፍ እንዳለበት ገልጸው ተሳትፎው በራሱ ውጤት የሚያመጣ እንዳልሆነ ይሞግታሉ፡፡ ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ጥቂት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ከፍተኛ ውጤት ሆኖ በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ግን እንብዛም ሊሆን ይችላል፡፡ በአንጻሩ በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ኖሯቸው በፈተና ወቅት የሚያስመዘግቡት ውጤት ግን አመርቂ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህን መሞገቻ ነጥብ በማንሳት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርሱ አሉ፡፡ ይህንኑ መነሻ ሀሳብ Nicols (1978)  የውጤት መለያየቱ በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ተላውጦዎች (የመምህሩ ልምድና ብቃት፣ የመማሪያ ዐውድ፣ የፈተናው ደረጃ፣ ወዘተ.) አንጻርም መታየት ስለሚኖርበት የ Marx & Marionን (1977) የምርምር ግኝት እንደማይቀበሉት ይጠቁማሉ፡፡ ይህም የተለያዬ አመለካከት በጥናት መረጋገጥ እንዳለበት

የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ ጥናትም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ተዛምዶ ምን እነደሚመስል ይመረምራል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት ትኩረት በተማሪዎች የክፍል ዉስጥ የትምህርት ተስትፎና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉጤት መካከል ያለዉን ግንኙነት መመርመር ነዉ፡፡ በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ያለዉ ተዛምዶ ብዙ ጊዜ ጥያቄ ይፈጥራል፡፡ በጥናቱ ዳራ ላይ እንደተገለጸው በውጭ ሀገሮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ግኝት ልዩነት ይታያል፤ መለያየቱ ደግሞ ለተጨማሪ ለጥናት የሚጋብዝ ነው፡፡ በተለይም ጥናቶቹ በተለያዩ ቋንቋዎችና ሀገሮች ላይ እንደመደረጋቸው በአማርኛ ቋንቋ ያለውን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት አጥኚ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ጥናቶችን ለማግኘት ባደረገው አሰሳ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለ ተሳትፎ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ የተደረገ ጥናት አልገጠመውም፡፡ በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ግን በርካታ ምርምሮች በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የበላይ (1992)፣ የለዘር (2004) እና የግዛቸው (2014) ጥናቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በላይ (1992) የ11ኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ምርምር ያደረጉ ሲሆን በጥናታቸው ግኝትም ሴት ተማሪዎች ያላቸው የተሳትፎ መጠን ዝቅ ማለቱን ጠቁመዋል፡፡ ለዘር (2004) በተመሳሳይ ጾታ ተኮር የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ ሴቶች ብቻቸውን የሚማሩባቸው እና ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በንጽጽር የተጠና ነው፡፡ በጥናቱ ውጤትም ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩት በተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡ ግዛቸው (2014) ደግሞ የተማሪዎች ተሳትፎን ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ በሚመለከት ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ግኝትም የማስተማሪ ዘዴዎችና የተማሪዎች ተሳትፎ ዝምድና እንዳለው አሳይተዋል፡፡

በዚህ ክፍል የተዳሰሱ ሶስቱም ጥናቾች በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ትኩረታቸውን ያድርጉ እንጂ ተሳትፏቸው ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ አላጠኑም፡፡ ለዚህ ጥናት መነሻ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱም ይህንን ክፍተት ለመሙላት በማቀድ ነው፡፡ በተጨማሪም አጥኚዉ በሥራ ላይ በቆየባቸዉ በርካታ አመታት በክፍል ዉስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት ንቁ ተሳትፎ የሌላቸዉ ብዙ የማይናገሩና የማይሰሩ በትምህርታቸዉ ከፍተኛ ዉጤት ሲያስመዘግቡና አንዳንድ ጊዜም የተሻለ ተሳትፎ ያላቸዉ ተማሪዎች በትምህርት ዝቅተኛ ዉጤት ሲያገኙ ተመልክቷል፡፡ ከሌሎች መምህራንም በዚሁ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ መረጃዎችን አግኝቷል፡፡ ይህም በጥናቱ ዳራ ላይ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የገለጹት ሀሳብ (የተማሪዎች ተሳትፎ ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖር) ጋር የሚጋጭ ልምድ ነው፡፡ ለዚህም ጥናት እንደሚያስፈልገው አጥኚው ስላመነ ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡ በተጨማሪም በበላይ (1992)፣ በለዘር (2004)

እና በግዛቸው (2014) ጥናቶች ከሴት ተማሪዎች ይልቅ የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ዝቅ ያለ እንደሆነ ጠቁመዋል። ከአጥኚው ተሞክሮ አንጻር ይህ የጥናት ግኝት በአሁኑ ዘመን ካለው ጾታን መሰረት ያደረገ ተሳትፎ አንጻር የተቃረነ ሆኖ አግኝቶታል። ይህንንም መነሻ ሀሳብ በጥናት ማረጋገጥ ስላስፈለገ ለአጥኚው መነሻ ሆኖታል።

## 1.3 የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ምላሽ እንዲፈለግላቸው የታሰቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ አለው?
2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ምን ያህል ነው?
3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ያሳያልን?

## 1.4 የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፤ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚያደርጉት የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከዉጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር፣
2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ እና
3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ የሚሉ ናቸው።

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎና የትምህርት ዉጤት ግንኙነትን መመርመር ለተማሪዎች፣ በትምህርቱ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ተቋማትና ለሀገር ጠቀሜታዉ ከፍተኛ ነዉ። መምህራን ተማሪዎቻቸው በክፍል ዉስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ተሳታፊ መሆን ወይም አለመሆን ከውጤት አንጻር የሚኖረውን ልዩነት እንዲያውቁ ያበረታታል።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል።

1. ለተጠኚ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ለሚከናወኑ የትምህርት ተሳትፎ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡
2. ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን የትምህርት ተሳትፎ ከትምህርት ውጤት ጋር ያለዉን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተዛምዶ በተመለከተ መረጃ ሊሰጣቸዉ ይችላል፡፡
3. መምህራን ምርምሩ በሚያስገኘዉ ዉጤት መሰረት ተማሪዎቻቸው ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን የማስተማር ዘዴና ልምድ ተገንዝበዉ የተሻለ ድጋፍ እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
4. በትምህርት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ ፖሊሲ አዉጪዎች፣ ዉሳኔ ሰጭዎችና ሌሎችም እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡
5. የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ተዛምዶን በተመለከተ ሰፋና ጠለቅ ያለ ጥናት ለማጥናት ለሚያቅዱ አጥኚዎች መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክፍል ዉስጥ ተሳትፎና የውጤት ተዛምዶ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚሸፍነው በኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን፣ ጊንጪ ከተማ በሚገኘው በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ይሆናል፡፡ የተማሪዎች ተሳትፎ በተለያዩ መንገዶች የሚገለጥ ቢሆንም በክፍል ዉስጥ የትምህርት ተሳትፎ ከሚገለጥባቸዉ መንገዶች በቃላዊ ተዋስኦዎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ጥናቱ የሚያተኩርባቸዉ ተለዋዋጮች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የተማሪዎቹ የክፍል ውስጥ የትምህርት ውጤት ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ ጥናቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ነጻ ተለዋዋጭ ሲሆን የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የትምህርት ውጤት ደግሞ ጥገኛ ተለዋዋጭ ይሆናል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃልና ሀረጋት ዐውዳዊ ብያኔ

ከዚህ በታች በምርምሩ ስራ በስፋት የሚጠቀሱና በስራ ላይ የሚዉሉ ቃላት ፍቺ ይቀርባል፡፡

**የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፡-** በክፍል ዉስጥ በተደጋጋሚ በተማሪዎች የሚከናወኑ የማዳመጥ፣ ጥያቄዎችን የመመለስ፣ ጥያቄዎችን የመጠየቅ፣ ለጥያቄዎች መልስ የመስጠትና በአጠቃላይ በክፍል ዉስጥ በሚደረጉ የግልና የቡድን ውይይቶችና ተግባሮችን ያካትታል፡፡ በዚህ ጥናት የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተመዘነው በአማርኛ ክፍለጊዜ በተደረገ ምልከታና በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡

**የተማሪዎች የትምህርት ውጤት፡-** የትምህርት ዉጤት ማለት አንድን የትምህርት ዓይነት በአላማው መሰረት መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለተማሪዎች

በማስተማር ትምህርቱ ከተላለፈ በኋላ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ የሚፈትሽና በተማሪዎች ላይ ያመጣውን የባህሪ ለዉጥ ተለክቶ የሚገኝ ዉጤት ነዉ። በዚህ ጥናት የተማሪዎች ውጤት የተመዘነው በአጥኚው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍና የመመህር መመሪያን መሰረት በማድረግ በተዘጋጀ የአማርኛ ፈተና ነው።

**ተዛምዶ፡-** ማለት በሁለቱ ተለዋዋጮች ማለትም በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎና ዉጤት መካከል የሚኖረዉን የግንኙነት መጠንና አቅጣጫ የሚያሳይ ነዉ። ለዚህም የፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

### 2.1.1 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምንነት

በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ ከሚደረግ የመምህር፣ ተማሪ፣ መማሪያ መጽሐፍ ተራክቦ ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ አንደኛው መከሰቻ ነው፡፡ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ደግሞ በአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ወቅት ግንባር ቀደሙን ሚና የሚወጣ ክንውን ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተቀምጠው መምህሩ ሲያስተምር ከማዳመጥ አልፈው በራሳቸው የሚማሩበት፤ ካላቸው ልምድ ጋር በማገናዘብ አዳዲስ ነገሮችን የሚያፈልቁበት ተግባር ነው፡፡ ተሳትፎ ተማሪዎች ተግባር ተኮር በሆነ መንገድ አዳዲስ ዕውቀት፣ አመለካከት፣ ልምድና ክህሎት የሚያዳብሩበት ሂደት ነዉ (Sitberman, 1996)፡፡

ለማ (1994) Block (1977)ን ጠቅሶ በክፍል ውስጥ በንግግር፣ በጽሁፍ፣ በንባብ፣ በማዳመጥና በማገናዘብ (Viewing) በሚሰጠው ትምህርት መካከል መደጋገፍ አለ፡፡ አንዱ ክሂል ሌላውን ክሂል ያጠናክራል፡፡ ኪነ-ቋንቋዎች (Langauge arts) በጣም የተሰናሰሉና እርስበርሳቸው በመደጋገፍ መሳለመሳ የሚያድጉ እንጂ በቅደም ተከተል ሥርዓት የሚሄዱ አይደለም በማለት ይገልፃል፡፡

ሁሉም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ አንድ አይነት ናቸው፡፡ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ሥራ፣ ጥናት ወይም ጨዋታ፣ ሀላፊነቶች፣ የሚኖሩበት ቦታ ወዘተ. አላቸው፡፡ በክፍል ውስጥ ግን የሚገኙት የራሳቸውን ስሞች፣ ዕውቀት፣ ልምድ፣ መረዳት፣ ክህሎት፣ ስሜት፣ ስብዕናና ሌሎች ነገሮችን ይዘው ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ ባህላዊና ትምህርታዊ ዳራ የላቸውም፡፡ ከዚህ አመክንዮ በመነሳት ሁለት ግለሰቦች አንድ አይነት ዕውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው እንደማይችል መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርቱን በመቀበል፣ ከመምህራን ለሚቀርቡ የተግባራት እንቅስቃሴና ክንውኖች የሚሰጧቸው ምላሾች አንድ አይነት ሊሆን እንደማይችል ያሳያል፡፡ ይህ ልዩነት በጾታ አቅጣጫም ሊታይ የሚችል ነው፡፡

በተጨማሪም የትምህርት ተሳትፎን በተመለከተ መምህራን የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን እና ክንውኖችን ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር በማቀናጀት የሚተገብሩ ከሆኑ ተማሪዎቹ በሚሰጠው ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎን በተመለከተ Thomas (1991) እንደሚያስረዱት ማንኛውንም ነገር ለመማር የግለሰቡ ብቃት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ቋንቋንም ለመማር የግለሰቡ ብቃት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም አካባቢውን በመታዘብ፣ በአማረ ቋንቋ የመግለጽ ክሂሎትን ይጠይቃል፡፡ ግን ይህ ግለሰባዊ ክሂል የሚከናወነው በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚማረውም ተማሪ በመምህሩ አሳታፊነት ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት፡፡ ይህም የሚያመለክተው በክፍል ውስጥ የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

በቋንቋ ትምህርትና በሌሎችም ያለውን የተማሪውን ተሳትፎ በሌላ መንገድ ተራክቦ በሚል ቃል መግለጽ እንደሚቻል Thomas (1991) ገልጸው ተራክቦ ባለሁለት ፈርጅ ሂደት (two ways process) እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህም አንድ ተናጋሪና አንድ አድማጭ ወይም ለንግግሩ ምላሽ የሚሰጥ አካል ያለበት ማለት እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በሁለትና ከዚያ ባላይ ባሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚደረግ ቃላዊ ምልልስ ወይም ንግግር ተራክቦ (ተሳትፎ) እንደሚባልም መረዳት ይቻላል፡፡ በክፍል ውስጥ በሚደረግ ተራክቦ ተሳታፊዎቹ መምህሩ፣ ተማሪዎችና የመማሪያ መጻህፍት መሆናቸው በተለያዩ ጥናቶች ተረጋግጠዋል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወን የመምህር ተማሪ ተራክቦ ሥር የሚነሱ ጉዳዮች ማለትም መምህሩና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተራክቦ የሚገለጸው በሚከተሉት ፈርጆች ዙሪያ ነው፡፡ እነዚህም ማስተማር፣ መጠየቅ፣ ማሞገስ፣ መተቸት፣ ናቸው፡፡ እንደ Allwright (1991) አገላለጽ ተራክቦ አንተ ለሰዎች የምታደርገው ነገር ሳይሆን ሰዎች በጋራ የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ለሚደረግ ተራክቦ የተማሪዎች ለመተባበር ወይም ላለመተባበር ያላቸው ምርጫ እና የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ለተራክቦ ስኬታማነት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የእርስ በእርስ ግንኙነቱ ስኬታማነት በራሳቸው በተማሪዎችና በመምህራን ህይወት ውስጥ ማህበራዊ ሁነት ነው፡፡ መምህራን የእርስ በርስ ግንኙነቱን ለሚመሩበት ሁኔታ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ በmortimore (1988) በእንግሊዝ በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት ተደጋጋሚ የሆኑ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ የሆነ ተጽዕኖ እንዳለው አሳይቷል፡፡ በእንግሊዝና በዌልስ በቅርብ የተደረገ ጥናት ደግሞ እንዳሳየው ተራክቦ ለውጤታማ ማስተማር ያለውን ጥቅም እንዲሁም ከፍተኛ የሆኑ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ መጠየቅ፣ ክፍት ጥያቄዎች መጠቀም፣ ተማሪዎች የራሳቸውን መልስ እንዲያብራሩ መጠየቅ፣ በክፍል ውስጥ የቀረበውን ትምህርት መሠረት አድረጎ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ግንኙነት እንዳለው Muijs (1999) ይገልጻሉ፡፡

Bronti (2018) እንደገለጹት ተሳታፊነት የተናጋሪነትን፣ ማህበራዊነትን፣ ነገሮችን ለማረጋገጥ መጣርን፣ ለሰዎች ፍቅር ማሳየትንና ለነገሮች በጎ ስሜት የማሳየት ባህርይን የሚመለከት ሰብእና ነው፡፡ የተሳታፊነት ሰብእና ያላቸው ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊነትን ለመፍጠር ብዙም አይቸግራቸውም፡፡ ይህም ደስታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ጭምትነት ግን ከዚህ በተቃራኒ ብቸኝነትን፣ ዝምታን፣ ለብቻ ራስን ችሎ መኖርንና መነጠልን የሚመርጥ የተሳታፊነት ተቃራኒ የሆነ ሰብእና ነው፡፡ ስለዚህ የተሳታፊነት ባህርይ ያላቸው ሰዎች በስራቸው ሁሉ ደስታን የሚያገኙት በማህበር ሲሰሩ ነው፡፡ ሌሎችን በማነቃቃትና በማጫወት ስራቸውን ውጤታማ ለማድረግ የሚጥሩ ናቸው፡፡ Zoltan (2005) እንደገለጹት አንድ ሰው የተሳታፊነት ደረጃው አስተማማኝ ሲሆን ተግባቢ፣ ፈጣን፣ ሰውን ወዳጅ፣ ምክንያታዊ፣ ተናጋሪና ጥንቁቅ ይሆናል፡፡ የተሳታፊነት ባህርይው ዝቅተኛ ሲሆን ደግሞ ዝንጉ፣ ቀለስላሳ፣ ንጥል፣ ሃሳብ የለሽ፣ ተጠራጣሪና፣ ቀዝቃዛ ሰብእና ይኖረዋል፡፡

ከላይ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ እንደተገለጸው ተራክቦ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል የሚያደረጉትን  የእርስ በርስ ግንኙነት ሲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩንና ተማሪዎችን፣ መማሪያ መጽሀፍቱን  እንዲሁም እነዚህ የሚደረጉትን የእርስ በርስ ግኑኝነት የሚመለከት ነው፡፡ በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ ተራክቦ በብዙ መንገድ-ይከናወናል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ ያስተምራል፣ ተማሪው ምላሽ ይሰጣል በዚህም-ጥያቄ ይጠየቃል፤ ይመልሳል፤ አስተያየት ይሰጣል፤ መምህሩ ለተማሪው በትምህርቱ ሂደት ለሚነሱ ጉዳዮች ምላሽ ይሰጣል፡፡ እነዚህም ማስተካከያ (እርማት፣ ማበረታቻ፣ ትችትና የመሳሰሉት) ናቸው፡፡

የትምህርት ተሳትፎ ለማስተማርና ተማሪዎችን ለማነቃቃት ወሳኝ ነው፡፡ መምህራን የትምህርት ተሳትፎን ማለትም በግል የሚደረገውን የትምህርት ተግባራትን በትብብር ከሚሰራው ጋር በማዋሃድና በጥያቄዎች ማሳደግ ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎችን በአጥጋቢ ሁኔታ የመጠየቅ ችሎታ ወሳኝ የሆነ የማስተማር ክሂል ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን ተሳትፎ ያሳድጋል፡፡ ውጤታማ ለመሆን በእያንዳንዱ ተማሪ ጥያቄዎች መጠየቅ፣ መረዳትና፣ መመለስ አለበት፡፡

ተማሪዎች በግል ከሚያደርጉት ተሳትፎ በተጨማሪ በጥንድ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ይህም የቡድን ሥራን ያበረታታል፡፡ ቀላል የሆነው የቡድን ሥራ አደረጃጀት ተማሪዎችን በጥንድ ማቀናጀትና ለእያንዳንዱ ሊያከናውኑት የሚችሉትን አእምሯዊ ተግባር መስጠት ነው፡፡ ይህን ተግባር Kegan (1989)ን ጠቅሰው Donald (1993)  የጥንድ ሀሳብ መካፈል (Think pair share) ይሉታል፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለ ትምህርቱ ይዘት እንዲያስቡ የሚገፋፋ እውቀታቸውን ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እንዲያነፃፅሩና መልሶቻቸውን በአጠቃላይ ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር እንዲለዋወጡ ያስችላል፡፡ ይህ ወደ ውጤታማነት ያደርሳል፡፡ Thomas (1987) እንደገለጹት ስኬታማ ተማሪዎች ተግባር ተኮር፣ በትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑና ተባባሪዎች ናቸው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደትም በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ የሚሰጧቸውን ሥራዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ያከናውናሉ፡፡

### 2.1.2 የክፍል ተሳትፎ ጠቀሜታ

Cohen (1991) እና Weaver & Qi (2005) በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ማሳተፍ በርካታ ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ይገልጻሉ፡፡ እንደCohen (1991) እና Weaver & Qi (2005) ገለጻ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተማሪዎች በትምህርት ተግባራት ንቁ እንዲሆኑ የሚያደርግ፣ የመማር ማስተማር ህይወት የሚሰጥ፣ ተማሪዎችን የበለጠ የሚያነሳሳ፣ የተሻለ እንዲማሩ የሚያደርግ እና ተማሪዎች የግል መረጃቸውን እንዲያቀርቡ የሚያበረታታ ነው፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎች የበለጠ የሚሳተፉ ከሆነ በትንሽ ትውስታ እንዲማሩ የሚያስችል፣ በከፍተኛ ደረጃ እንዲገናዘቡ የሚያደርግ፣ አንድን ነገር እንዲተነትኑ፣ እንዲያጠቃልሉ፣ ሀሳብን አያይዘው እንዲገልጹ የሚያግዝ እና የንግግር ክህሎታቸውን እንዲሻሻል የሚረዱ መሆኑን Brown (1994) እና Smith (1992) ይገልፃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በስፋት የተለማመዱበትንና በንቃት የተሳተፉበትን የትምህርት ይዘት በተሻለ ሁኔታ ሊገነዘቡት እንደሚችሉ Bailey & Savage (1994) ያስረዳሉ። በተመሳሳይ Fassinger (1995) እንደጠቀሱት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ከሆነ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩና በትምህርት ውጤታማ እንደሆኑ ያግዛል። በመማር ማስተማር ሂደት የክፍል ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች አዲስ ክህሎትን እንዲማሩ ወሳኝ የሆኑ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል፤ የመማር ጠቃሚ የሆኑ ጥልቅ ትርጉም የሆነው ተዛምዶ በአዕምሮ ውስጥ እንዲፈጠርም ይረዳል። Weaver & Qi (2005) እንደገለጹት የክፍል ተሳትፎ ተማሪዎች በቀጣይ ምን መማር እንዳለባቸው እንዲያስቡና እንዲገልጹ እድል የሚሰጥ በመሆኑ የመማር ማስተማር ዓላማን ለማሳካት ያስችላል። በተመሳሳይ Hill (2007) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ቢያደርጉ የትምህርት ይዘቱን የበለጠ እንዲያገናዝቡና ትምህርቱን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ የሚያግዝ መሆኑን ይገልፃሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Petress (2000) የተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንዲማሩና እንዲያስታውሱ እንደሚያስችላቸው ይገልጻሉ። ምክንያቱም ተማሪዎች የተሻለ ሊማሩ የሚችሉት በመስራትና በመሳተፍ እንዲማሩ ሲደረግ ነው። እንዲሁም መማር ሳቢና ማራኪ የሚሆነው ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ንቁ ተሳትፎ ሲኖራቸው ነው። በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት በጥያቄና መልስ፣ አስተያየት በመስጠት፣ በመወያየት እና በመተቸት እንዲሳተፉ ማድረግ ለተማሪዎች እና መምህራን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ገለጻ መረዳት ይቻላል።

### 2.1.3 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መከሰቻዎች

የቋንቋ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ክፍል የራሱ የሆኑ ዓላማዎችና ይዘቶች አሉት። ከሌሎች የሚለይበትም ዋና ነጥብ ቃላዊ የሆነ ተግባቦትን በስፋት መጠቀሙ ነዉ። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማጎልበት ነዉ። እነዚህ ክሂሎች ሊዳበሩ የሚችሉት ተግባራዊ በሆነ የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ነዉ።

Allwright (1991:19) በክፍል ውስጥ ለሚደረጉ የትምህርት ተሳትፎዎች የትኩረት አቅጣጫዎች በሚከተሉት ጥያቄዎች እንደሚከሰቱ ይጠቁማሉ።

1. ማን ነው የሚናገረው?
2. ስለምን ይናገራሉ?
3. እያንዳንዱ ተሳታፊ በሚያገኛቸው በርካታ እድሎች ምን ያከናውናል?
4. በክፍል ውስጥ ምን አይነት የመማር ማስተማር ድባብ ተፈጥሯል?
5. ምን አይነት የቋንቋ አጠቃቀም አለ?

ይህ ጥናት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎ ከትምህርት ውጤት አንፃር ያለውን ተዛምዶ መመርመር አብይ የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ የተነሳ በመሆኑ በዚህ ክፍል ላይ የተጠቀሱት የትምህርት ተሳትፎ በተለይም የRena & Doolars (2011) እና Allwright (1991) ንድፈ ሀሳቦችን ይከተላል።

እንደ Allwriright & kathleen (1991) በመምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመገመትና በተመራማሪዎች የምልከታ መረጃዎች ላይ ብቻ በማተኮር መካከል ልዩነቶች አሉ። መምህራን በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን መጠቀም በቂ እንዳልሆነ ይገምታሉ። ለመምህራን የዐይን ግንኙነት፣ እጅ ማውጣት፣ የሚሰማ ቃላዊ ምልልስ፣ ራስን ማንቀሳቀስ፣ ወዘተ. የተማሪዎችን የተሳትፎ መጠን ለመዳኘት ይጠቀሙበታል። ይህም ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ተነሳሽነት ውጪ የራሳቸውን ውሳኔ ለመስጠት ሁሉም ዓይነት የተሳትፎ ቅርፆች የሚታዩ አይደሉም። በቋንቋ ትምህርት ተግባራት በተወሰነ ሁኔታ በአብዛኛው መልኩ ውስጣዊ የአእምሮ ክስተት የማይታዩ ጉዳዮች ናቸው። ለዚህም የጽሑፍ መጠይቅ አስፈላጊ ነው።

እውቀት አዕምሯዊ ክንዋኔ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ላይገለጽ ይችላል። እንደ Norris (1972) አገላለጽ ትምህርትን መማርና ትምህርትን የመማር ችሎታ የተማሪዎች ውስጣዊ እንቅስቃሴ ውጤት ነው። ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎች አዕምሮ ብቃትንም ይጠይቃል። እንዲህ ሲባል ግን እነዚህ የግድ መታየት አለባቸው ማለት አይደለም። ተማሪው ምናልባት በክፍል እንቅስቃሴ ሲያደርግ ሊታይ ይችላል። ይህ ግን ተማሪውን ከሌሎች በተለየ የተሻለ አድርጎ ለማሳየት አይደለም።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖር ተሳትፎ የሚከናወነው ብዙ ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች (ተማሪዎች ከተማሪዎች ወይም ተማሪ(ዎች) ከመምህር) መካከል የሚደረግ ተራክቦ ነው። በተራክቦው ውስጥ ደግሞ ተግባቦት አለ። Nunan (1993) የተግባቦቱ ዓላማ በመማር ማስተማሩ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ ካለ ግልጽ እስኪሆን ድረስ የሚኖርን ተዋስኦ የሚመለከት እንደሆነ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ Sunderland (1994) በተራክቦ ተናጋሪና አድማጭ ሊኖር እንደሚችልና በሁለቱ መካከል የሚኖር መስተጋብር ተራክቦ እንደሆነ ያስረዳሉ። በመሆኑም የክፍል ተሳትፎ በአዳማጭና በተናጋሪ (በመምህርና በተማሪ ወይም በተማሪና በተማሪ) መካከል የሚደረግ የሀሳብ ልውውጥ ነው። በመሆኑም የክፍል ውስጥ ተሳትፎም በሚኖረው የሀሳብ ልውውጥ የሚለካ ይሆናል። ይህም በተለያዩ መልኮች ሊከሰት የሚችል ነው። ብዙ ጊዜ ተሳትፎው በማስተማር (መምህሩ)፣ ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት በመስጠት፣ በመተቸት እና በማሞገስ ይገለጻል።

### 2.1.4 የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ደረጃ መለኪያ

የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎን በተመለከተ Thomas (1991) እንደሚያስረዱት ማንኛዉንም ነገር ለመማር የግለሰቡ ብቃት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ቋንቋንም ለመማር የግለሰቡ ብቃት አስፈላጊ ነዉ። ይህም አካባቢዉን በመታዘብ በአማረ ቋንቋ የመግለጽ ክህሎትን ይጠይቃል። በአመዛኙ ይህ ክሂል የሚከናወነው በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። በክፍል ውስጥ የሚማረውም ተማሪ በመምህሩ አሳታፊነት ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት፤ ይህም የሚያመለክተው በክፍል ውስጥ የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ያህል አስፈላጊ እደሆነ ነዉ።

የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በክፍል ውስጥ ያሉ የመማር ማስተማር ሂደቶችን በጥልቅ በመመርመር መለካት የሚችል ሲሆን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የማስተማሪያ ዘዴና ተማሪዎችም ከማስተማሪያ ዘዴው ጋር ያላቸው መስተጋብር የተሳትፎውን መጠን ያሳያል፡፡ ብዙ ጊዜ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርገው መምህሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ሲተገብር ነው፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎችም በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴውን በመተግበሩ ረገድ የሚያሳዩት ምላሽ ያላቸውን ተሳትፎ ያሳያል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ዘዴዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

#### 2.1.4.1 በውይይት የማስተማር ዘዴ የሚያሳዩት ተሳትፎ

ውይይት በተማሪዎችና በመምህራን ወይንም በተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል በአንድ የትምህርት ይዘት ላይ የሚደረግ ነፃ የሆነ የመረጃ፣ የሀሳብና የአስተያየት ልውውጥ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ግንዛቤያቸው እንዲጨምርና ችግራቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲፈቱ ከማስቻሉ በተጨማሪ ተፈላጊ የሆነ አመለካከትን ለማዳበር ጉልህ ሚና ይጫወታል (Byrne, 1987)፡፡

ውይይት አብሮ የመስራት ክህሎትን ለማዳበርና ችግሮችን የሚፈቱ ዜጎች ለመፍጠር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ርዕስም ሆነ አዲስ የሆነ ርዕስ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገምገም ይጠቀሙበታል (Sensan, 1997)፡፡ ውይይት በተለያዩ ቅርጾችና እና ስልቶች ለክሄድ ይችላል፡፡

**የጥንድ ውይይት፦** ከክፍለ ጊዜው ትምህርት ጋር በተያያዘ ርዕስ ላይ ሁለት ተማሪዎች በጋራ በመሆን የሚያካሂዱት የውይይት አይነት ሲሆን በአብዛኛው በአጭር ጊዜ የተለያዩ ሃሳቦችን ለማግኘት ይረዳል፡፡ ይህ ዘዴ መምህር ተኮር ዘዴን አሳታፊ ለማድረግም ያገለግላል (Doff, 1988)፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች የተጠቀሰውን ጉዳይ በተገቢውና በታዘዙት መልኩ ሀሳብ ሲለዋወጡ ተሳትፎ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

**የትንንሽ ቡድኖች ውይይት፦** ከ4-6 የሚሆኑ ተማሪዎችን በአባልነት የያዙ ከአስር ደቂቃ ያልበለጠ ውይይት የሚከናወንበት የውይይት አይነት ነው (Cruickshank, 1999)፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች የሚያሰጡት ሀሳብ እና ያላቸው ተሳታፊነት የተሳትፎ መጠናቸውን ይለካል፡፡

**የፖናል (የተተኳሪ ቡድን) ውይይት፦** አንድን ርዕስ ወስዶ ባለሙያ ክፍል ውስጥ በመጋበዝ የሚካሄድ የውይይት አይነት ነው (Farrant, 1980)፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች የሚያውቁትን ሀሳብ ያለምንም ፍርሀት ሲገልጹ ዕይታቸውንና ተሞክሯቸውን ሲያጋሩ ተሳትፏቸው ይታያል፡፡

**የሴሚናር ውይይት፦** የተመረጡ ተማሪዎች በአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ዝግጅት ወይም ጥናት አድርገው ያገኙትን ውጤት ለተማሪዎቹ ካቀረቡ በኋላ የሚደረግ የውይይት አይነት ነው (Moore, 2001)፡፡ በዚህ ወቅት ሀሳባቸውን፣ አድናቆታቸውን፣ አስተያየታቸውን በሚሰጡት መጠን ተሳትፏቸውንም መለካት ይቻላል፡፡

**መፍትሄ ማቅረብ ላይ ያተኮረ ውይይት፦** ከክፍለ ጊዜው ትምህርት ጋር የተያያዘ አንድን ጉዳይ በጥያቄ መልኩ በማንሳት ተማሪዎች በቡድን ሁነው የተለያዩ የመፍትሄ ሃሳቦች እያፈለቁ የሚያካሂዱት የውይይት አይነት ነው (Jonsen, 2007)፡፡ በዚህ ወቅትም በሚያነሷቸው የመፍትሄ ሀሳቦች እና ሁሉም ተማሪዎች ባላቸው ተሳትፎ የተሳትፎ ደረጃቸው ይወሰናል፡፡

መምህሩ የውይይት የማስተማሪያ ዘዴን ሲመርጡ ተማሪዎች ደግሞ እንዲሁ የውይይቱን መመሪያ ተከትለው ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ በሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎም የተሳትፎ ደረጃቸው ይወሰናል፡፡

### 2.1.4.2 በክርክር ወቅት የሚኖር የተማሪዎች ተሳትፎ

በክርክር የማስተማሪያ ዘዴ ከውይይት የማስተማር ዘዴ ጋር ተመሣሣይ ሆኖ አቀራረቡ በርካታ ህጎች ያሉት ነው፡፡ ክርክር አመለካከትን መሰረት ያደረገ ጥያቄ በማንሳት በሁለት ወገኖች መካከል የሚካሄድ ትምህርታዊ ሙግት ሲሆን ብዙ ጊዜ የተሳታፊዎችን የማዳመጥ የማሳመን እና በቃል የመግለጽ ክህሎትን ለማሳደግ የሚረዳ ዘዴ ነው (Cochan, 1989)፡፡ በዚህም የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ሲሳተፉ የተሳትፎ መጠናቸውም በዚያው መጠን ይለካል፡፡

### 2.1.4.3 በድራማ ማስተማር

አንድ ልቦለዳዊ ድርሰትን ወይም በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ተውኔትን መሰረት ያደረገ ትወና ማካሄድን ያሳያል፡፡ ድራማ ማስመሰል ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ከሚና ጨዋታ የተለየ ልምምድ፣ ጊዜ እና ቁሳቁስ ይጠይቃል፡፡ ድራማን ያለድምጽ በእንቅስቃሴ ብቻ እንዲሁም ድምጽ እና እንቅስቃሴን በማዋሃድ በሁለት መልኩ ማካሄድ ይቻላል (Dhand, 2004)፡፡ በዚህም ትግበራ ተማሪዎች የሚኖራቸው ተሳታፊነት የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ይወስናል፡፡

### 2.1.4.4 በትንሽ ቡድን ማስተማር ዘዴ የሚኖራቸው ተሳትፎ

ይህ ዘዴ ቁጥራቸው አነስተኛ ለሆኑ ተማሪዎች የሚመረጥ የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ የአመራርና የማስተማር ብቃቶችን ለማዳበርም ተመራጭ የሆነ ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም ግን በመሀል በመሀል ተማሪዎችን የሚያሣትፉ እንቅስቃሴዎች መኖር አለባቸው፡፡ ከክፍለ ጊዜው በፊት ለተማሪዎች ክፍለ ጊዜውን የሚመሩት እነሱ መሆናቸውን፣ የሚያስተምሩበትን ርዕስ፣ ምን ያህል ሰዓት እንዳላቸውና ርዕሱን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው መንገር ያስፈልጋል፡፡ የአመራርና የማስተማር ብቃቶችን ክፍለ ጊዜ ከ10-20 ደቂቃዎች ቢወስድ ጥሩ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን የተሰጠው ርዕስ እና ያሉት የተማሪዎች ቁጥር ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ በመጨረሻ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስለአቀራረቡ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል (Bonwell and Eison 1991)፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘዴ ተማሪዎች የሚኖራቸው ትግበራ ተሳትፏቸውን ይለካል፡፡

#### 2.1.4.5 በጥያቄና መልስ የሚኖራቸው ተሳትፎ

ጥያቄና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን አንድ ርዕስ ጉዳይን ለማስተማር ሲጀምሩ በመግቢያ ላይ የተማሪዎቻቸውን የቀደመ ዕውቀት ለመረዳትና ያለፈውን ትምህርት ለመከለስ፤ በመሃከል ላይ ደግሞ ተማሪዎቻቸው የዕለቱን ትምህርት ምን ያህል እየተከታተሉ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚጠቀሙበት፤ በመጨረሻ ላይ የክፍለ ጊዜው ትምህርት ዓላማ ከግቡ መድረሱንና አለመድረሱን ለመገምገም ለተማሪዎቻቸው ጥያቄ በማቅረብ ምላሽ የሚቀበሉበትና የተማሪዎቻቸውን አቅም የሚመዝኑበት የአሳታፊ የማስተማሪያ ስልት ነው (Nunan 1988)። በዚህ ወቅት ተማሪዎች የሚሰጡት መልስ ያላቸውን የተሳትፎ ደረጃ ያሳያል።

#### 2.1.4.6 አሳታፊ ባልሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎች ተሳትፎ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የተማሪዎች ተሳትፎ ለመለካት የሚያመቸው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በክፍል ውስጥ ሲተገበር ነው። ሆኖም ግን መምህሩ የመረጠው ዘዴ አሳታፊ ባይሆንም የተማሪዎችን የተሳትፎ ደረጃ መወሰን ይቻላል፡፡ በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ በዋናነት ተማሪው ያልገባውን ሀሳብ ጥያቄ በመጠየቅ ወይም በተማሩት ትምህርት ላይ አስተያየት በመስጠት ሊለካ ይችላል።

በአጠቃላይ የተማሪዎች ተሳትፎ ጎልቶ እንዲታይና የተሳትፎ መጠናቸውን መለካት ይቻል ዘንድ መምህሩ የሚከተለው የማስተማሪያ ዘዴ ተጽዕኖ አሳዳሪ ነው። ለዚህም ግዛቸው (2014) የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶን በተመለከተ ምርምር አድርገው በመካከላቸው አዎንታዊ ዝምድና እንዳለ መግለጻቸው አስረጂ ነው። ከዚህ ባሻገር ትምህርት በሚቀርብበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት በንቃት የሚሳተፉበትንና የሚካፈሉበትን ጊዜ በመመልከት ተሳትፏቸውን መለካት ይቻላል (Rena & Doorlars, 2011)። ትምህርቱ መሰጠት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎች አስተማሪውን እያዳመጡ ወይም አስተማሪው የሚሰራውን እየተመለከቱ ስለሚሆን ተማሪዎች በሥራ ላይ ናቸው። ማለትም የመምህሩን ጥያቄ እየመለሱ፣ እያነበቡ ወይም እየጻፉ ናቸው። እንደ Rena B.hawrs and Donald-H- Doorlars (2011፡97) ገለፃ በቋንቋ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረጉ የትምህርት ተሳትፎዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች ማካተት ይኖርባቸዋል።

- ✓ **የክንውን ጊዜ**፡ ማለት ተማሪዎች አንድ ነገር በሚያከናውኑበት ጊዜ በንቃት የሚሳተፉበትን ጊዜ፣ መጠንና ስፋትን ይመለከታል።
- ✓ **የመምህሩ ጥያቄዎችና የተማሪዎች ምላሾች፡** በትምህርቱ ሂደት በመምህራን የሚጠየቁ የጥያቄ ዓይነቶችና ተማሪዎቹ የሚመልሱበት ዘዴ ወይም መንገድ
- ✓ **ተማሪዎች ጥንድ ሆነው ሲሰሩ የሚኖራቸው የተሳትፎ ክንውን**፡ ተማሪዎች በጥንድ ስራዎችን የሚያጠናቅቁበት መንገድ፣ ስራውን ሲያከናውኑ የሚሰጧቸው ምላሾችና የሚጠቀሙበት የቋንቋ ዓይነት
- ✓ **የክፍል ውስጥ መስተጋብር፡**የመምህር ተማሪና የተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት

- ✓ የቡድን ሥራ ለቡድን ሥራ ተሳትፎ የሚኖረው ጊዜና በቡድን ሥራዎች የሚታየው ትጋት
- ✓ **ተግባራት፡**- በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውናቸው ሥራዎችንም በተመለከተ በደንብ ማዳመጥ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ የእርስ በእርስ ግኑኝነት፣ የበጎ ፍቃደኝነት መልሶች
- ✓ ተማሪዎች ስላለፈው ጊዜ ትምህርት የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማጠቃለያ ዘገባዎች
- ✓ ተማሪዎች በፊት ስለተማሩት ትምህርት ወይም የቤት ስራዎች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች
- ✓ ተማሪዎች እርስ በእርስ ሊጠያየቁ ይችላሉ፡፡ ወይም መምህሩ የክፍሉን ተማሪዎች ሊጠይቅ ይችላል፡፡
- ✓ የግል ሥራ፡- ይህ በአጠቃላይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በስፋትና በድግግሞሽ ሥራ ላይ የሚውል የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህም የሚያካትተው እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ የግል የጥያቄ ወረቀቶችን (work sheet) መስራት፣ ምንባብ ማንበብ፣ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ ከመፅሐፍ ላይ መልመጃዎችን መሰራት፣ ድርሰትን መፃፍ፣...... ወዘተ ነው፡፡

በመማሪያ ክፍል ያለው የክንውን ጊዜ ላይ በብዛት ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ Richards (1996)፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት Richards (1996:15) በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡

1. የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነቃቃ እና የሚገነባ በመሆኑ
2. ተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ላይ እንዲያስቡና እንዲያተኩሩ የሚያበረታታ በመሆኑ
3. ተማሪዎች የጠየቁትን ወይም የተናገሩትን መምህሩ እንዲያብራራ ስለሚያደርግ
4. መምህራን የተማሪዎችን መረዳትና ግንዛቤ እንዲያረጋግጡ ስለሚያስችላቸው
5. በትምህርቱ ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ ስለሚያነቃቃ የተሳትፎ ጊዜ ሲጨምር ትምህርቱም ስለሚጨምር ነው፡፡

በመሆኑም ጥያቄዎችና ለጥያቄዎች የሚሰጡ ምላሾች በተሳትፎ መለኪያነት ትልቁን ሚና የሚጫወቱ ይሆናል፡፡

## 2.2 የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ

የክፍሉ ውስጥ የትምህርት ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ግንኙነት ትምህርት ውጤት አብረው የሚታሰቡ ነገሮች ናቸው፡፡ አንዱ ከሌላው ሊነጠል አይችልም፡፡ Kauchak & paul (1993) እንደሚያስረዱት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች በትምህርት ተሳትፏቸው ከ75% እና ከዚያ በላይ እንደ ሆኑና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎ 50% እና ከዚያ በታች እንደ ሆነ ነው፡፡ Everston, et al. (1980) እና Fredrik (1977) ይህም የትምህርት ተሳትፎ በውጤት ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እንዳለው በመግለጽ የKauchak & paul (1993)ን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡

McGeeal (1985) የክፍል ዉስጥ የትምህርት ጊዜ ከተሳትፎና ከዉጤት ጋር የተያያዘ እንደሆነና ተማሪዎች ብዙ በተሳተፉ ጊዜ ውጤታቸዉ እየጨመረ እንደሚሄድ

በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ በMcGeeal (1985) ጥናት እንደ ተረጋገጠዉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜያት በንቃት የሚሳተፉ ተማሪዎች 80% ዉጤታማ እንደሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም Slavin (2018) የተሻለ ስኬት ማግኘት ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩና እንዲበረታቱ እንደሚያደርግ ይጠቁማሉ፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ብዙ በተሳተፉ ቁጥር ውጤታቸውም የዚያኑ ያህል ከፍ እንዲል ሊያደርግ ይችላል፡፡

Amidon (1976) በአንድ ክፍል ዉስጥ ሰፋ ባለ የጥያቄና መልስ ሂደት የሚሳተፉ ተማሪዎች በመጠኑ ከሚሳተፉ ተማሪዎች የበለጠ የመቀበል ችሎታ እንዳላቸው፣ ዉጤታቸዉም የተሻለ እንደ ሆነ በጥናታቸው አረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ Tony (1987) እንደገለጹት ተማሪዎች በውጤት የተሻሉ ተማሪዎች ለመሆን በመማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊና በሚሰጣቸዉ ሥራ ላይ ዉጤታማ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የክፍል ዉስጥ ሂደት መምህሩንና ተማሪዉን የሚያሳትፍ በመሆኑ ተማሪዎችም ይህም ሂደት እንዲሟላ የሚጠበቅባቸዉን ነገር ማከናወን አለባቸው፡፡

Stevenson & Joy (1994) እንደገለጹት አንዳንድ ተማሪዎች ምናልባት ጥረትና ችሎታ ቀጥተኛ ዝምድና አላቸዉ ወደሚለው አመለካከት ሊመጡ ይችላሉ፡፡ እና ዉጤት ከፍተኛ የሆነ ጥረትና ተሳትፎን ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተማሪዉ ችሎታ ያንሰዋል ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተሞክሮ የተማሪዎችን በብቃት ላይ ያላቸዉን አመለካከት ሊለዉጠዉ ይችላል ማለት ነዉ፡፡

መምህራን አንድ ማወቅ ያለባቸው ነገር የተማሪው የመማር ስልት ከመምህራን የማስተማር ስልት ጋር ሁልጊዜ በትይዩ ላይሄድ ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዲውም አንዱ ከሌላው የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ጥቂት ተማሪዎች ዝምታን በመምረጥ ለመማር ማዳመጥ ይመርጣሉ፡፡ ነገር ግን መምህራን በመናገር ይማራሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ከዚያም በክፍል ውስጥ የጥቂት ተማሪዎች የሚታይ ቃላዊ ግንኙነት ደረጃ ከራሳቸው አመለካከት ጋር የተገናኘ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም በተሻለ ሁኔታ ጋር በተወሰነ መልኩ ደግሞ ተማሪዎች ለመናገር ይፈልጉ ይሆናል፤ ግን ይህን ለማድረግ ደግሞ ይፈራሉ፡፡ ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተማሪዎቹ የትምህርት ውጤት ላይ አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ አለው፡፡ skinner (1985) የተማሪዎች ባሕሪ፣ ስብእና የተለያዩ ተግባራት፣ የአከባቢ ሁኔታና የመሳሰሉት ጉዳዮች በተማሪው ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገልጻል፡፡

## 2.3 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚው ባደረገው ዳሰሳ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና በተመለከተ ያጠና አጥኚ ማግኘት አልቻለም፡፡ ሆኖም ግን የተማሪዎች ተሳትፎ የሚመለከቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም

መካከል አጥኚው የበላይ (1992)፣ የለዘር (2004)፣ የጎርፍነሽ (2011) እና የግዛቸው (2014) ጥናቶችን ዳሰሳ አድርጎባቸዋል፡፡

በላይ (1992) "የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱን ለማጥናት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው መዳህኒዓለም አጠቃላይ ትምህርት ቤት 79 ወንድ እና 68 ሴት ተማሪዎችን በናሙናነት የመረጡ ሲሆን የጽሑፍ መጠይቅና ምልከታን ነው፡፡ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ተተንትነው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት እንዳለ ያመለከቱ ሲሆን ከፍ ያለ ተሳትፎ ያደረጉትም የወንድ ተማሪዎች እንደሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ የበላይ (1992) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በማጥናት ላይ በማተኮሩ ሲሆን የሚለየውም የበላይ (1992) ጥናት ተሳትፎውን የወንዶችን ከሴቶች ጋር በማነጻጸር ላይ የተጠና ነው፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ የወንድም ሆነ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከአማርኛ ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና የሚመለከት በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በክፍል ደረጃ የተለያየ መሆን፣ የጥናት ዘመኑ መራራቅ በጥናቶቹ መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል፡፡

የለዘር (2004) ጥናት ደግሞ "በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውንና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርትቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አድርገዋል፡፡ ለጥናቱ የልደታ ማርያም የልጃገረዶች ትምህርት ቤትና የልደታ ማርያም የወንዶች (ወንዶችና ሴቶች አብረው የሚማሩበት) ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ከዘጠነኛ ክፍልም ሴቶች ብቻ ከሚማሩበት ትምህርት ቤት 113፣ ሴቶች ከወንዶች ጋር አብረው ከሚማሩበት ትምህርት ቤት ደግሞ 51 (በድምሩ 164 ሴት ተማሪዎች) ተመርጠዋል፡፡ መረጃዎችም በምልከታ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩት በተሻለ መጠን ተሳትፎ እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ የለዘር (2004) ጥናት ከበላይ (1992) ጥናት ጋር በሴቶች ተሳትፎ ላይ በማጥናታቸውና በአዲስ አበባ ላይ በማተኮራቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ የለዘር (2004) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በማተኮሩና በተሳትፎ ላይ በመጠናቱ ተመሳሳይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መጠቀሙ ያመሳስለዋል፡፡ የሚለያዩበት ደግሞ የለዘር (2004) ጥናት ልክ እንደ ዳዊት (1992) ጥናት በሴቶች ተሳትፎ ላይ በማተኮሩ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የተማሪዎች ተሳትፎ ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ያጠናል፡፡

የጎርፍነሽ (2011) ጥናት ደግሞ "አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የክፍል ተሳትፍ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ትንተና (በዲውሮ ዞን ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አድርገዋል፡፡ ለጥናቱ በዳውሮ ዞን በሶስት የመንግስት ትምህርትቤቶች 171 ተማሪዎችን አካተዋል፡፡ መረጃ የተሰበሰበው ደግሞ በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ ነው፡፡ በጥናቱ ውጤትም በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች እንዳሉ

ጠቁመዋል። ከእነዚህ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ የተማሪዎች ውጤት ዝቅ ማለት በተሳትፏቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የገለጹት ይጠቀሳል። ይህም በተማሪዎች ውጤትና በተሳትፏቸው መካከል ዝምድና ሊኖር እንደሚችል የሚጠቁም ግኝት ነው። ከዚህ ጥናት ጋር በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መመሳሰልና በተሳትፎ ላይ ትኩረትን በማድረግ ምስስሎሽ ይታያል። ልዩነታቸው ደግሞ የጎርፍነሽ (2011) በተግዳሮት ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን ተሳትፎ ከውጤት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚያጠና ነው። በተጨማሪም በጥናት ዘመንና ቦታ መለያየትም ከዚህ ጥናት ይለየዋል።

በመጨረሻም የግዛቸው (2014) ጥናትን እንመልከት። ጥናቱ "ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት (በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተደረገ ነው። ለጥናቱ በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ ኢየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል የሚማሩ 90 ወንዶችና 90 ሴቶች በድምሩ 180 ተማሪዎችን መርጠዋል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ናቸው። በጥናቱ ውጤትም የመምህራን ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ተሳትፎ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው ተመላክቷል። ይህ ጥናት ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንጻር ከዚህ ጥናትና የለዘር (2004)፣ የጎርፍነሽ (2011) እና የግዛቸው (2014) ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል። ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን መከተሉና የአማርኛ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከሌላ ተላውጦ ጋር ማዛመዱነው። የግዛቸው (2014) ጥናት ተሳትፎን ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ሲያጠና ይህ ጥናት ግን ተሳትፎን ከውጤታቸው ጋር ማዛመዱ ያለያያቸዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ በአይነቱ መጠናዊ ሲሆን ገላጭ ተዛምዷዊ ንድፍን በመከተል ተከናውኗል፡፡ ገላጭ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተለዋዋጮች መካከል ሊኖር የሚችልን የግንኙነት አቅጣጫና መጠን ለመወሰን የሚያስችል ነው (ያለው፣ 2009)፡፡ በመሆኑም በተዛምዶ ንድፍ የሚጠኑት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎና ዉጤት ናቸዉ፡፡ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ዝምድና ለመለካትም ፒርሰን የተዛምዶ ስሌት መለኪያ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በተዛምዶ ስሌቱ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በምርምሩ የተገኘው የተዛምዶ ስሌት ውጤት (-1 እስከ 1 ያለውን የስሌት ውጤት) ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተዛምዶ ጥናት መሰረት 0 ዝምድና አለመኖርን ሲያመለክት ከ 0 ወደ -1 ወይም 1 እየተጠጋ ሲሄድ ደግሞ የተዛምዶ መጠኑን ከፍ እያለ መሄዱን ያሳያል፡፡ ወደ -1 እየተጠጋ ከሄደ ዝምድናው አሉታዊ ሲሆን ወደ 1 እየተጠጋ ከሄደ ደግሞ ዝምድናው አዎንታዊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሁለቱ ተላውጦዎች የተዛምዶ ሁኔታ፣ የተዛምዶ መጠንና አቅጣጫ ተወስኗል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

በመረጃ ምንጭነት የተመረጠው ትምህርት ቤት ጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የትምህርት ሥራው የሚከናወነው በ2015 ዓ.ም 9ኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች እና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው ክፍለጊዜዎች የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ሆነው አገልግለዋል፡፡

## 3.3 ናሙናና የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1 የትምህርት ቤት እና የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት የተመረጠው ትምህርት ቤት በኦሮምያ ክልል፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን በደንዲ ወረዳ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች መካከል የጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠው በአመች የንሞና ስልት ነው፡፡ አመች የንሞና ስልት ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት አጥኚዉ ከሚሰራበት ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝና ለመረጃ አሰባሰቡ የተሻለ አመቺ ሁኔታ ይኖራል በሚል መነሻ ነው፡፡

ለጥናቱ የተመረው የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት 9ኛ ክፍል አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያው (ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን አጠናቀው ወደሌላኛው እርከን የሚገቡበት) ስለሆነ ነው፡፡ ይህም ለቀጣይ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ክፍሎች መነሻ ስለሆነ የጥናቱ ውጤት ለትምህርት ስራው

ያበረክተዋል ተብሎ የሚታሰበው አስተቀዋፅኦ ለቀጣይ ክፍሎች ጭምር እንዲረዳ ታስቦ የተመረጠ ነው፡፡

### 3.3.2 የተማሪዎችና የመምህር ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚመለከታቸው በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት 51 ነው፡፡ የሚማሩት በአንድ መማሪያ ክፍል ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ለጥናቱ ስለሚያስፈልጉና ንሞና ለመውሰድ የሚያስገድድ ባለመሆኑ በጠቅላይ የንሞና ዘዴ (Comparehensive Sampling) መሰረት በሙሉ ተማሪዎች ለጥናቱ ተወስደዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የጥናቱ ዋና አላማ በተማሪዎች የክፍል ዉስጥ የትምህርት ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለዉን ተዛምዶ መመርመር ስለሆነ የተማሪዎችን የክፍል ዉስጥ የትምህርት ተሳትፎና ዉጤት ማወቅ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ለዚህም የተመረጡት አግባብነት ያላቸው ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በክፍል ዉስጥ በአጥኚው የሚደረግ የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ናቸው፡፡

### 3.4.1 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምልከታ

Benneft & Namara (1979) የምልከታ መርሀግብሮች ለበርካታ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በመግለጽ ከነዚህም አንዱ በክፍል ዉስጥ ባሉ ተግባራትና በተማሪው ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ BLaws & H-Doorlag (2011) የመማሪያ ክፍልን ባህርይና የጥናት ክህሎትን ለማጥናትና መረጃ ለመሰብሰብ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ዘዴ ምልከታ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መነሻነት ይህ ጥናትም በክፍል ውስጥ ያለውን የተማሪዎች ተሳትፎ ለመመርመር የክፍል ውስጥ ምልከታን ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪ ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲሳተፉ (ጥያቄ በመጠየቅ፣ ምላሽ በመስጠት፣ የክፍል ሥራ በመስራት፣ ወዘተ.) ተግባራዊ የሚሆንና ሊታይ የሚችል በመሆኑ ለዚህ ጥናት የተዋቀረ ወይም የተደራጀ ምልከታ (Structured Observation) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ስምንት ክፍለ ጊዜዎችን ለመረጃ መሰብሰብያነት ተጠቅሟል፡፡

የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ምልከታ የተካሄደዉ በክለሳ ድርሳናት ላይ በተዳሰሱ ንድፈሀሳባዊ ተግባራት አማካይነት ነው፡፡ የትምህርት ተሳትፎ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ጥያቄ የመጠየቅና ከመምህሩ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን የግልና የቡድን ሥራን መስራትን ያጠቃልላል፡፡ የክፍል ዉስጥ የትምህርት ተሳትፎ በአንድ አጥኚ በምልከታ በክፍል ዉስጥ በማንኛዉም ጊዜ የሚከናወኑ ድርጊቶችን ለምሳሌ (/) በመጠቀም መረጃውን ሊሰበስብ ይችላል (David, 1985)፡፡ አጥኚው በስራ ላይ ያዋለውም ይህንኑ ዘዴ ነው (የተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ ከአባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቁ የተዘጋጀበት ዓላማ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የተዘጋጀውም በአጥኚው ሲሆን እንደመነሻ የሆኑት በምዕራፍ ሁለት ላይ የተዳሰሱ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያዎች ናቸው፡፡ በውስጡም የተካተቱበት የጥያቄዎች ብዛት 22 ሲሆኑ ሁሉም የሊከርት ስኬልን መሰረት አድርገው ተዘጋጅተዋል፡፡ 22 ጥያቄዎች በአራት ምድብ የተከፈሉ ሲሆን በምድቦቹ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች ብዛት በጥያቄና በአስተያየት መልኩ የሚታዩ 5 ጥያቄዎች፣ በጥንድ ወይም በቡድን ውይይት መልኩ የሚታዩ 6 ጥያቄዎች፣ የክፍል ተግባራት ላይ ያለ ተሳትፎን የሚመለከቱ 6 ጥያቄዎች እና በጽብረቃ (Presentation) መልኩ የሚታዩ 5 ጥያቄዎች ናቸው (የተዘጋጀው መጠይቅ ከአባሪ 1 ይመልከቱ)፡፡

የመጠይቁን ትክክለኛነት ለመፈተሽ በጥናቱ አማካሪና የክፍል ደረጃውን በሚያስተምሩ መምህራን ታይቶ አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን አስተማማኝነቱን ለመፈተሽ ደግሞ የክፍል ደረጃቸው በሚመሳሰሉ በሀጫሉ የሁለተኛ ደረጃ 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የፍተሻ ጥናት (Pilot Study) ተደርጓል (በፍተሻ ጥናቱ የተሰበሰበው መረጃ ከአባሪ 5 ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም በሙከራ ጥናቱ የተገኘው ውጤት በክሮንባኽ አልፋ ስሌት ተሰልቶ $\alpha$= 946 ሆኗል (የስሌቱ ዝርዝር መረጃ ከአባሪ 8 ላይ ይመልከቱ)፡፡ ይህም ከ.7 በላይ በመሆኑ መጠይቁ ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡

### 3.4.3 የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የተማሪዎችን ውጤት በሰነድ ፍተሻ ከተማሪዎች የውጤት ማጠራቀሚያ ቋት መሰብሰብ ይቻል ነበር፡፡ ግን በፈተና ጥያቄዎች የክብደትና የቅለት ደረጃ፣ የመለየት ብቃት፣ የአስተማማኝነትና የይዘት ተገቢነት ችግሮች አንጻር ሊመጡ የሚችሉ ውጫዊ ተጽዕኖዎችን ለመቆጣጠር ፈተናው በአጥኚው ተዘጋጅቶ ቢፈተኑ ተመራጭ ይሆናል ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

ፈተናው የተዘጋጀው በአጥኚው ሲሆን ተተኳሪ ተማሪዎች ፈተናውን የተፈተኑት በየካቲት ወር ላይ በመሆኑ የመጀመሪያው ወሰነትምህርት ወቅት በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት ሁሉም የትምህርት ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች እንደተሰጣቸው የክብደት ደረጃ ታይቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት የጥያቄ ማውጫ ቢጋር (Item Spesfication) ቀድሞ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚያም ትክክለኛነቱን ለመፈተሽ በሚያስተምሩት መምህራንና በጥናቱ አማካሪ በማሳየት የይዘትም ይሁን የቋንቋ እርማት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም የፈተናውን ትክክለኛነት ከፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

የፈተናውን አስተማማኝነት፣ የቅለትና ክብደት ደረጃ እና የመለየት ብቃት እና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ሀጫሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የፍተሻ ጥናት (Pilot Study) ተደርጓል፡፡ በሙከራ ጥናቱ 30 ተማሪዎች የተዘጋጀውን ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ፈተናው ቁርጠኛ ምላሽ የሚሰጠው በመሆኑ በአጥኚው

ታርሞ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቧል (በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበው መረጃ ከአባሪ 6 ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም የጥያቄዎች የክብደትና ቅለት ደረጃ (Level of Difficulty) ተለይቷል፡፡ በዚህም መሰረት 2 ቀላል (0.77 እና በላይ)፣ ቀሪዎቹ 48 ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት (ከ0.40 እስከ 0.76) ሆነው በመገኘታቸው ከቀላል እስከመካከለኛ ጥያቄዎች እንደተካተቱ አመልክቷል (የእያንዳንዱ ጥያቄ የክብደት ደረጃ ከአባሪ 7 ይመልከቱ)፡፡

የጥያቄዎች የመለየት ብቃት (Item Discrimination) በሙከራ ጥናቱ ወቅት ከ30 ተማሪዎች በተሰበሰበው መረጃ ተሰልቷል፡፡ በስሌቱ መሰረት የተገኘው ውጤት ሁሉም ጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከ0.33 እስከ 0.78 ባለው ተገኝቷል፡፡ ይህም ውጤት የበለጠ ወደ1 እየቀረበ የሚሄድ በመሆኑ የጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከመካከለኛ እስከከፍተኛ እንደሆነ አሳይቷል (የእያንዳንዱ ጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከአባሪ 7 ይመልከቱ)፡፡ አስተማማኝነቱን ለመፈተሽ ደግሞ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ $\alpha$ = .923 ውጤት ተገኝቷል (የፍተሻ ጥናቱ አስተማማኝነት ዝርዝር ስሌት ከአባሪ 9 ይመልከቱ)፡፡ ይህም ከፍተኛ አስተማማኝነት እንዳለው ስለሚያመለክት ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡

## 3.5 የመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች

በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በአጥኚው ነው፡፡ በመጀመሪያ የተሰበሰበው መረጃ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (በምልከታ) ነው፡፡ አጥኚው ለምልከታው በትምህርት ቤቱ ይሁንታ ለማግኘት ፈቃድ በመጠየቅ ይሁንታን አግኝቷል፡፡ ከዚያም ተጠኚ ተማሪዎችን የሚያስተምረው መምህር ፍቃደኝነት ተጠይቆ ፍቃደኛ ሆኗል፡፡ በምልከታዉ ሂደት ለጥናቱ የተመረጡ ተጠኚዎችን በማስተዋልና በጥንቃቄ በመከታተል መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ተጠኚዎች ለጥናቱ ሥራ ሲባል ቋሚ የሆነ የመቀመጫ ቦታና ለእያንዳንዳቸው ስማቸዉንና መለያ ቁጥራቸዉን የያዘ ካርድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለተዛምዶ አገልግሎት እንዲውሉና ከመጠይቁና ከፈተናው ጋር በትይዩ እንዲቀመጡ የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በተናጥል መለየት በማስፈለጉና አቀማመጣቸው የሚገኘው የተማሪዎችን መለያ ኮድ በመረዳት ምልክት ለማድረግ ስለሚረዳ ነው፡፡

ከዚያም በ3.4.1 እንደተገለጸው የምልከታ ቅጹ በአራት ክፍሎች ተዋቅሮ ከተዘጋጀ በኋላ የተማሪዎች የተሳትፎ ትግበራ ድግግሞሽ በእያንዳንዱ ተማሪ አንጻር (/) ምልክት በማስቀመጥ ተሞልቷል፡፡ በእያንዳንዱ የምልከታ ቀናት አንድአንድ የምልከታ ቅጽ የተሞላ ሲሆን በስምንት ክፍለ ጊዜዎች የተሞላው ቅጽ አንድ ላይ የድግግሞሽ ቆጠራ ምዝገባን ተግባራዊ ተደርጓል (የድግግሞሽ ቆጠራው ውጤት ከአባሪ 10 ይመልከቱ)፡፡ ከአራት ዋናዋና መስፈርቶች ውስጥ ሁለቱ (ውይይት እና የክፍል ውስጥ ትግበራ) የሁሉንም ተማሪዎች በአንዴ ለመመልከት ስለሚያስቸግር በድምጽወምስል አጋዥነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በምልከታ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ በጽሑፍ መጠይቅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ተሰብስቧል፡፡ አሞላሉን በተመለከተ ተማሪዎቹ እንዳይቸገሩ ከመሙላታቸው በፊት በአጥኚው አጭር ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመቀጠል የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ለመፈተሽ የተዘጋጀላቸውን ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ተማሪ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ ያስመዘገበው ውጤት ተደምሮ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የሚኖርን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲወክል ተደርጓል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናው ውጤት ደግሞ በአጥኚው ከታረመ በኋላ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን እንዲወክል ተደርጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ከተሳትፎ ውጤቱ በትይዩ እንዲሰፍር ተደርጓል (የተሳትፎና የአማርኛ ቋንቋ ውጤት መረጃ ከአባሪ 11 ይመልከቱ)፡፡

በጥናቱ ንሞና አመራረጥ እንደተጠቆመው የተጠኚዎች ብዛት 51 ነበር፡፡ ሆኖም ግን አንድ ተማሪ በትምህርት ገበታው ላይ ባለመገኘቱ (በማቋረጡ) እና ሁለት ተማሪዎች መረጃዎችን በተገቢው መልኩ ባለመሙላታቸው ከጥናቱ ወጥተዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የተደረገው በ48 ተማሪዎች መረጃ ነው፡፡

## 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች (3.5) እንደተገለጸው በትምህርት ተሳትፎና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር በመጀመሪያ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እና በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተደምረው የተገኘው ውጤት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ተፈትነው ያገኙት ውጤት የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን እንዲወስን ተደርጎ ውጤቱ በጥንቃቄ ተሞልቷል፡፡ በአሞላል ወቅት ስህተት እንዳይፈጠር ሁለት መምህራን የተሞላውን ውጤት በትክክል ስለመሞላቱ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚያም የተሞላው መረጃ SPSS Version 26 መተግበሪያ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation Cofficient)፣ የቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) እና የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Indipendant Samples T-Test) ተተንትኗል፡፡

በትምህርት ተሳትፏቸው እና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ስሌቱ የተካሄደውም ስለሁለቱ ተላውጦዎች በተገኙት ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ በባለሳጥን ግራፎች (Boxplots) ተሰርተው (አባሪ 15 ይመልከቱ) ከተፈተሹ በኋላ ነበር፡፡ በተጨማሪ ሁለቱ ተላውጦዎች ያላቸው ግንኙነት በብትን ግራፍ (Scatterplot) ተሰርቶ አንጻራዊ በሆነ ዕይታ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው (አባሪ 17 ይመልከቱ) ከታወቀ በኋላ ነበር፡፡

የተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን ከመተንበይ አኳያ ያለውን ድርሻ ለማወቅ የቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) ትንተና ተካሂዷል፡፡ ለዚህ ስሌትም ተንባይ ተለዋዋጩ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሆኖ ሲወሰድ ተተንባይ ተለዋዋጩ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ሆኖ የቀላል ድህረት ስሌቱ ተሰልቷል፡፡ የተንባይ ተለዋዋጩ ድርሻም ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በተጋርቶት መጠን መለኪያ (Coefficient of Determination-$R^2$)

ተፈትሿል፡፡ የተንባይ ተጽእኖውን ጥንካሬ ለማወቅም መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (Standardized Regeration Coefficient- β) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የቀላል ድህረት ስሌት ከመከናወኑ በፊትም እሙኖቹ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ የመጀመሪያው እሙን የናሙና መጠን ሲሆን Pituch & Stevens (2016:123) ለማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ጥናት ለእያንዳንዱ ተንባይ (ነጻ) ተላውጦ 15 የናሙና መጠን በቂ እንደሆነ በገለጹት መሰረት አንድ ተንባይ ያለው ይህ ጥናት 48 የናሙና መጠንን መሰረት አድርጎ መሰራቱ እሙኑ እንዳልተጣሰ አመላካች ነው፡፡ ሌላው እሙን በተላውጦዎቹ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት (Linearity) መኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን ተንባይ ተላውጦ የሆነው የተማሪዎች የአማርኛ ክፍለጊዜ ተሳትፎ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ 0.642 ያህል ዝምድና ስላሳየ እሙኑ መሟላቱ ተረጋግጧል፡፡

የስህተት መጠን ስርጭት (Homoscedasticity) እሙን መሟላቱን ለመፈተሽ ቀሬ ውጤቶቹ (standardised residual) በብትን ግራፍ ላይ በz-Predicted እና በz-residual መካከል ባለ ግንኙነት ተፈትሿል፡፡ በአባሪ 18 እንደተመላከተው የስህተት መጠኖች አንድ ላይ የተከማቹ ባለመሆናቸውና አንጻራዊ በሆነ እይታ ተበትነው የሚታዩ በመሆናቸው እሙኑ እንደተሟላ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህም ሌላ በተካሄደው የስርጭት ወጥነት ፍተሻ (Tests of Normality) የአማርኛ ትምህርት ፈተናው ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ (Z value for the Skewness) ዋጋ 0.985፤ የዝብጠት መጠን የዜድ (Z value for Kurtosis) ዋጋ ደግሞ -0.798፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ ዋጋ 1.92፣ የዝብጠት መጠን የዜድ ዋጋ -1.42፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ ዋጋ 1.725፣ የዝብጠት መጠን የዜድ ዋጋ -0.391 ሆነው ተገኝተዋል (አባሪ 12 ይመልከቱ)፡፡ እነዚህ የሾጣጣነትና የዝብጠት የዜድ ዋጋዎች ደግሞ መጠናቸው ±1.96 ($P< 0.05$) ርቀት ውስጥ የሚካተቱ በመሆናቸው ውጤቶቹ ወጥ ስርጭት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም እሙኖች እና መደበኛ ሥርጭት መሟላታቸው በመረጋገጡ የመረጃ ትንተናው ፓራሜትራዊ ቴስት በሆነው በድህረት ትንተና ተተንትኗል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ማሳየት አለማሳየታቸውን ለመፈተሽ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ተደርጓል፡፡ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ከመሰላቱ በፊት የሴትና የወንድ የአማርኛ ትምህርት መረጃዎችና የክፍል ውስጥ መረጃዎች የቲ-ቴስት ዋና እሙን የሆነውን መደበኛ ስርጭት (Normal Distribution) ማሟላታቸው በሻፒሮ-ዊልክ አማካይነት ተፈትሿል፡፡ በሻፒሮ-ዊልክ የተፈተሸበት ምክንያትም በእያንዳንዱ ቡድን (ሴትና ወንድ) ያሉት ተጠኚዎች ብዛት ከ50 በታች በመሆኑ ነው፡፡ የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት እንዲሁም የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት መረጃዎች የሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ ውጤት $P>0.05$ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ሶስቱም መረጃዎች በሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ እሙኑን እንዳሟሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት መረጃዎች በሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ ግን እሙኑን አሟልተው ባለመገኘታቸው ($P<0.05$) የበለጠ ፍተሻ

እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በግድለት (skewness) እና በዝብጠት (Kurtosis) መደበኛ ውጤቶች አማካይነት ተጨማሪ ፍተሻ ተካሂዶባቸዋል፡፡ የግድለት (1.519) እና የዝብጠት (- .749) መደበኛ ውጤቶቹም በ-1.96 እና በ1.96 መካከል በመገኘታቸው እሙኑ መሟላቱን ለመረዳት ተችሏል (የመደበኛ ስርጭት ፍተሻ ውጤቶቹ ከአባሪ 13 እና ከአባሪ 14 ተመልቷል)፡፡ በተጨማሪም የነጻ ናሙና ስሌቱ የተካሄደውም በሴትና በወንድ ቡድኖች በተገኙት ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ በባለሳጥን ግራፎች (Boxplots) ተሰርተው (አባሪ 16 ይመልከቱ) ከተፈተሹ በኋላ ነበር፡፡ መረጃዎቹ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረታዊ እሙን የሆነውን የስርጭት ወጥነት እንደሚያሟሉ በተገለጸው መንገድ ከተፈተሹ በኋላ በነጻ ናሙና ስሌት ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

ከዋናው የጥናቱ ዓላማ በመነሳት ይህ ጥናት የመለሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ሶስት ናቸው፡፡ በ3.6 እንደተገለጸው ለሶስቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ በቀላል ድህረታዊና በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ በኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ አለው?" የሚል ሲሆን የተማሪዎች ተሳትፎ በምልከታ በተማሪዎች መጠይቅ፣ የተማሪዎች ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በፐርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ትንታኔው በሰንጠረዥ 4.1 ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ**

| ተላውጦ (Variable) | የናሙና ብዛት (No.) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | ተዛምዶ (Pearson Correlation) | | ጉልህነት (Sig. (2-tailed)) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | የትምህርት ውጤት | |
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | 48 | 64.63 | 30.53 | 1 | .642** | .000 |
| የትምህርት ውጤት | 48 | 30.38 | 8.34 | .642** | 1 | .000 |

**ጉልህ ተዛምዶ በ0.01 ደረጃ (ባለ 2-ጫፍ)

በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመላከተው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የተማሪዎች የተሰበሰበው ከ48 ተማሪዎች ነው፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ለመወሰን የተፈተኑት ፈተና ከ50 ነጥብ ታርሞ ተማሪዎቹ ያገኙት አማካይ ውጤት 30.38 ነው፡፡ ይህም ውጤት ከአጋማሽ ውጤት (25) ከፍ ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የትምህርት ውጤታቸው መደበኛ ልይይት ደግሞ 8.34 ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ከአማካዩ (30.17) በ8.34 ያህል እንደሚርቁ ያሳያል፡፡ ከተገኘው የመደበኛ ልይይት ውጤት በመነሳት ተማሪዎች ተቀራራቢ ውጤት እንዳስመዘገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ለመፈተሽ በምልከታ የተገኘው ውጤትና በመጠይቅ የተገኘው ውጤት በእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ ተደምሮ የተገኘው አማካይ ውጤት 64.63 ነው። በምልከታ የተገኘው ውጤት የሚወክለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ባደረጉት መጠን በምልከታ ቅጹ አማካይነት የተሳትፎ የድግግሞሽ መጠኑ ተደማምሮ የተገኘ ነው (በምልከታ የተገኘው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ ውጤት ከአባሪ 6 ይመልከቱ)። በዚህ መሰረት የተገኘው አማካይ ውጤት 14.52 ነው። የመጠይቁ ውጤት ደግሞ ከ110 ያህል ነጥብ ተቆጥሮ የተገኘው ውጤት የተገኘው አማካይ ውጤት 51.29 ሆኖ ተመዝግቧል (ውጤቱ ሲመዘገብ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በአሉታዊ መልኩ የተገለጹ ገለጻዎች ግልብጥ ኮድ ተደርገው ተመዝግበዋል)። የሁለቱ ድምር (የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤት) 64.63 የሆነው በዚህ ሂደት ነው።

የክፍል ውስጥ ተሳትፎው መደበኛ ልይይት 30.53 ነው። ይህም ተተኳሪ ተማሪዎች ከአማካይ ውጤቱ (64.63) በ30.53 እንደሚርቁ የሚያሳይ ነው። የተገኘው የመደበኛ ልይይት ውጤት ከአማካዩ ወደግማሽ የሚቀርብ በመሆኑ በተማሪዎች መካከል የተሳትፎ መለያየቱ የጎላ እንደሆነ ያመለክታል።

የተተኳሪ ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት r=.642፣ P<.01 (ባለሁለት ጫፍ) ነው። ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች (በተተኳሪ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት) መካከል ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ያሳያል። መጠኑ ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ Dornyei (2007) ባስቀመጡት መስፈርት አማካይነት መረዳት ተችሏል። የተዛምዶው መጠንና አቅጣጫ የተለየው በፒርሰን ተዛምዶ ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት (ከ 0 እስከ -1/+1) Dornyei (2007) እና ያለው (2009) ባቀረቧቸው መስፈርቶች መሰረት ነው። በመሆኑም ተዛምዶው አዎንታዊ ቁጥር ማስመዝገቡ ተዛምዶው አዎንታዊ መሆኑን ሲያመለክት የተዛምዶው መጠን ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ እና ይህም ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ (P<.01) መሆኑን የትንተናው ውጤት ያሳያል።

### 4.1.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ምን ያህል ነው?" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት መረጃዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በምልከታና በመጠይቅ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስበው በቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) ትንተና ተተንትኗል። የትንታኔው ውጤት በሰንረዥ 4.2 ይመልከቱ።

**ሰንጠረዥ 4.2፤** የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን የመተንበይ ድርሻ፣ በቀላል ድህረት

| ተላውጦዎች | የተጋርቶ መጠን ($R^2$) | ድህረታዊ መጣኝ (B) | መደበኛ ስህተት (Standard Error) | መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (β) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢተለዋዋጭ (Constant) | .412 | 19.034 | 2.204 | | 8.636 | .000 |
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | | .175 | .031 | .642 | 5.680 | .000 |

ተንባይ ተላውጦ፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ
ተተንባይ ተላውጦ፤ የትምህርት ውጤት

በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመላከተው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የመተንበይ ድርሻ ለመፈተሽ በተደረገው ትንተና በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አዎንታዊ የላቀ የመተንበይ ድርሻ እንዳለውና የመተንበይ ድርሻው በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ያሳያል። የትንበያ ውጤቱ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ ያለው ልዩነት (variance) 41.2% ($R^2$ = .412) ያህሉ በበአማርኛ ቋንቋ ትምህር በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሊገለጽ እንደሚችል የሚያሳይ አንድምታ አለው።

ነጻ ተላውጦው በአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመመርመር በመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ ስሌት ተሰልቷል። የድህረታዊ መጣኝ ስሌቱ እንደሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (ነጻ ተለዋዋጩ) በአንድ አሀድ መጨመር የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ በ.175 ያህል እንዲጨምር ያደርገዋል የሚል አንድምታ ይሰጣል። ይህም ውጤት በስታቲክስ ጉልህ እንደሆነ (p = .000) ያሳያል።

### 4.1.3 የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት የጾታ ልዩነት

የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ያሳያልን?" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘትም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ያለን የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በምልከታና በተማሪዎች መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እና የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስቦ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Indipendant Sample T-Test) ተተንትኗል። በመጀመሪያ የተማሪዎች

የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ቀጥሎም የአማርኛ ቋንቋ ውጤት እንደየቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል፡፡ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የጾታ ልዩነት በሰንጠረዥ 4.3 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3፤** በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተላውጠ (Variable) | ጾታ (sex) | ብዛት (n) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ (df) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | ሴት | 25 | 67.92 | 33.634 | 46 | .776 | .442 |
| | ወንድ | 23 | 61.04 | 27.055 | | | |

በሰንጠረዥ 4.3 እንደተመላከተው የ25 ሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤት 67.92 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት ደግሞ 61.04 ነው፡፡ ይህም የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት በ6.88 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ መደበኛ ልይይት ከወንድ ተማሪዎች መደበኛ ልይይት በ6.579 ይበልጣል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች (በሴትና በወንድ) መካከል ጉልህነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም በተደረገው የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት የተገኘው ውጤት t (46) = .776, p = 0.442 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት P>0.05 በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሴትና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4፤** የአማርኛ ቋንቋ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተላውጠ (Variable) | ጾታ (sex) | ብዛት (n) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ (df) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአማርኛ ትምህርት ውጤት | ሴት | 25 | 30.72 | 9.977 | 46 | .301 | .765 |
| | ወንድ | 23 | 30.00 | 6.317 | | | |

በሰንጠረዥ 4.4 እንደተመላከተው የ25 ሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት 30.72 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት ደግሞ 30.00 ነው፡፡ ይህም የሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት በ0.72 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የሴት

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መደበኛ ልይይት ከወንድ ተማሪዎች መደበኛ ልይይት በ3.66 ይበልጣል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች (በሴትና በወንድ) የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም በተደረገው የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሴት የተገኘው ውጤት t (46) = .301, p = .765 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት $P>0.05$ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሴትና የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ በውስጡም ሶስት ንዑሳን ዓላማዎችን መርምሯል፡፡ ሶስቱንም ንዑሳን ዓላማዎች ለመመርመር የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲሁም በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መፈተሽ የጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተፈትሿል፡፡ ከዚያም ፈተናዎቹ በአጥኚው ታርመው የተማሪዎችን ውጤት እንዲወክሉ ከተደረገ በኋላ የምልከታውና የመጠይቁ መረጃ ደግሞ ተደማምሮ የአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን እንዲወክል ተደርጎ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ በቀላል ድህረታዊ እና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ንዑስ ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው "አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚያደርጉት የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከዉጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር" የሚል ሲሆን ተዛምዷቸውን ለመመርመር የተሰበሰቡ መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትነዋል፡፡ በትንታኔው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ($r=.642$፣ $P<.01$ (ባለሁለት ጫፍ)) እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የተዛምዶ መጠኑ ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ Dornyei (2007) ባስቀመጡት መስፈርት አማካይነት መረዳት ተችሏል፡፡

በአንደኛው ንዑስ ዓላማ የተገኘው የዚህ ጥናት ውጤት Kauchak & paul (1993) ካስረዱት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች በትምህርት ተሳትፏቸው ከ75% እና ከዚያ በላይ እንደ ሆኑና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎ 50% እና ከዚያ በታች እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡ Kauchak & paul (1993) ከገለጻቸው በመነሳት የትምህርት ውጤትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተዛምዶ እንዳላቸው የገለጹ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ዐውድም ተመሳሳይ ውጤት እንዳለ የሚያሳይ በመሆኑ ጥናቱ Kauchak & paul (1993) ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡ በተመሳሳይ በMcGeeal (1985) ጥናት እንደ ተረጋገጠዉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜያት በንቃት የሚሳተፉ ተማሪዎች 80% ዉጤታማ ከገለጹት እና Slavin (2018) የተሻለ ስኬት ማግኘት

ተማሪዎች የበለጡ እንዲሰሩና እንዲበረታቱ እንደሚያደርግ ከጠቆሙት ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ይመሳሰላል፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛ ዓላማ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፌት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ” የሚል ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በቀላል ድህረታዊ ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው ውጤትም ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መጨመር ወይም መቀነስ ያለው ተጽዕኖ የላቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

Stevenson & Joy (1994) በቋንቋ መማር ማስተማር ዐውድ ተሳትፎ ከሌለ የተማሪዎች ውጤትም ሊቀንስ እንደሚችል ከገለጹት ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡ በተመሳሳይ Borich (2004) በመማር ሂደት የተማሪዉ ተሳትፎ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና ለውጤታቸው ከፍ ማለት ወይም ዝቅ ማለት የሚያበረክተው አስተዋጽዖ የላቀ እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት ሶስተኛ ዓላማ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፌት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ” የሚል ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ ምላሽ ለማግኘት በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች የወንድና የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤቶች ለየብቻ ተሰልተው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ በትንታኔው ውጤትም በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ 25 ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤት 67.92 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት ደግሞ 61.04 በመሆኑ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት በ6.88 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ ይህም ከወንድና ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳትፎ ያደረጉት ሴት ተማሪዎች ናቸው የሚያስብል ውጤት ከገላጭ ስታትስቲካዊው መረጃ መረዳት ቢቻልም ይህ ውጤት ስታቲካዊ ጉልህነት መኖር አለመኖሩ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መፈተሽ አለበት፡፡ የወንድና የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤቶች በስታቲካዊ ጉልህነታቸው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተገኘው አማካይ ውጤት ስታትስቲካዊ ጉልህ አለመሆኑን (t (46) = .776, p = 0.442) ነው፡፡ በመሆኑም ከነጻ ናሙናው ትንታኔ በመነሳት የሴት ተማሪዎችና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

የሴት የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው እና የወንድ ተማሪዎች ውጤታቸው ያለውን ልዩነትም እንዲሁ ፍተሻ ተደርጎበታል፡፡ በዚህም መሰረት በአጥኚው ተዘጋጅቶ ተጠኚ ተማሪዎች ከ50 ነጥብ በተፈተኑት ፈተና 25 ሴት ተማሪዎች ያገኙት አማካይ ውጤት 30.72 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት ደግሞ 30.00 በመሆኑ የሴት ተማሪዎች ውጤት በ0.72 ውጤት እንደሚበልጥ የሚያሳይ ነው፡፡ የገላጭ ስታትስቲክስ መረጃው ተቀራራቢ እንደሆኑ የሚያሳይ ሲሆን ስታትስቲካዊ ጉልህ መሆናቸውን ለመፈተሽ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻው የተገኘው አማካይ ውጤት  እንደሚያመለክተው የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ($t$ (46) = .301, $p$ = .765) አለመኖሩን ነው፡፡

በቀደምት ጥናቶች ቅኝት እንደተመላከተው በሴትና በወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ጥናቶቹ የተገኙ ግኝቶች ግን ከዚህ ጥናት ግኝት ጋር የማይደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በላይ (1992) የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በሚመለከት ባደረጉት ጥናት የተማሪዎችን ተሳትፎ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን ሰብስበው ባደረጉት የትንታኔ ውጤት በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት እንዳለ ያመለከቱ ሲሆን ከፍ ያለ ተሳትፎ ያደረጉትም የወንድ ተማሪዎች እንደሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ በዚህ ጥናት ውጤት የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ሴትና ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ልዩነት አለመኖሩን በማመልከቱ የውጤት መለያየት ታይቷል፡፡

ለዘር (2004) ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውንና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርትቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በንጽጽር ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤት ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው የተማሩት ሴት ተማሪዎች ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅ ያለ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን በዚህ ጥናትም ሴትና ወንድ ተማሪዎች ተቀላቅለው የሚማሩበት ትምህርት ቤት ላይ ጥናት የተደረገ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ግን የተመጣጠነ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ይህም የለዘር (2004) እና የዚህ ጥናት ውጤት የተለያዩና የማይደጋገፉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም መለያየት ሴት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፤ ይህን ዋና ዓላማ በሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች አማካይነት ተመርምሯል፡፡ መረሰታዊ ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ አለው?

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ምን ያህል ነው?

3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ያሳያልን?

ለሶስቱም መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት መጠናዊ ምርምር ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ ተዛምዶውን ለመፈተሽ በ2015 ዓ.ም. ጊንጫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ 48 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ከ48 ተማሪዎች መረጃ የተሰበሰበው በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ያለ ተሳትፎ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ እና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ መጠይቅ ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአጥኚው በተዘጋጀ ፈተና ተሰብስቧል፡፡ የምልከታ ቅጹ፣ መጠይቁና ፈተናዎቹ መረጃ ለመሰብሰቢያነት ከማገልገላቸው በፊት በአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ታይተው የይዘትና የቋንቋ ማስተካከያ ተሰጥቷቸው ትክክለኛነታቸውን ከፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ አስተማማኝነታቸውን ለመፈተሽ ደግሞ የፍተሻ ጥናት (Pilot Study) ተደርጎ የመጠይቁም የፈተናውም መረጃዎች በክሮንባኽ አልፋ ተሰልተው የተገኙ ውጤቶች $\alpha > .7$ ሆነዋል፡፡ የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ደግሞ የክብደትና ቅለት ደረጃ፣ የመለየት ብቃታቸው ተፈትሾ አስተማማኝ ሆነው በመገኘታቸው መረጃ ለመሰብሰብ አገልግለዋል፡፡

የተሰበሰቡ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ከሰፈሩ በኋላ በገላጭ ስታትትሲክስ፣ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ በቀላል ድህረት እና በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነው የሚከተለውን ውጤት አስገኝተዋል፡፡

1. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ($r=.642$፣ $P<.01$፣ ባለሁለት ጫፍ) እንዳለ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ፍተሻው አሳይቷል፡፡ እንደሆነ ያለው (2009) እና

Dornyei (2007) ባስቀመጡት መስፈርት መሰረት የተዛምዶ መጠኑ ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል።

2. ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አሳይቷል። ይህም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መጨመር ወይም መቀነስ ያለው ተጽዕኖ የላቀ መሆኑን ያሳያል።

3. የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተገኘው አማካይ ስታትስቲካዊ ጉልህ አለመሆኑን (t (46) = .776, p = 0.442) ነው። በመሆኑም ከነጻ ናሙና ቲ-ቴስቱ ትንታኔ በመነሳት የሴት ተማሪዎችና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል።

4. የሴት እና የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ልዩነት ተፈትሾ የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት (t (46) = .301, p = .765) አለመኖሩን በጥናቱ ተረጋግጧል።

## 5.1 አስተያየት

ከጥናቱ ትንታኔና ከጥናቱ ግኝት በመነሳት አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርቧል።

1. በጥናቱ ግኝት እንደተመላከተው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ያላቸው ተዛምዶ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ነው። የተዛምዶ መጠናቸውም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ቢያበረክቱ፤

2. በጥናቱ ግኝት መሰረት እንደተገለጸው የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ትምህርት ውጤታቸውን የመተንበይ ድርሻው ከፍተኛ ነው። ይህም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከፍ እንዲል ለማድረግ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከፍ ማድረግ ያለው አስተዋጽዖ ከፍ ያደርጋል የሚል አንድምታ አለው። በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ተማሪዎችም እንዲሳተፉ በማነቃቃትና አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን በመከተል ተሳትፏቸውን እንዲጨምር ቢያደርጉ፤

3. የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና የትምህርት ውጤት ካላቸው ከፍተኛ ዝምድና አንጻር ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸውን በማሳደግ ውጤታቸውን ማሳደግ

እንዲችሉ የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች መማሪያ መጻሕፍትንና የመምህር መምሪያዎችን ሲያዘጋጁ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ምቹ የሆነና የሚያበረታታ እንዲሆን ትኩረት ቢያደርጉ፤

4. በጥናቱ ግኝት እንደተገለጸው የሴትና የወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ በአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው ተመጣጣኝ ናቸው። ሆኖም በቀደምት ጥናቶች ቅኝት እንደተገለጸው፣ በጥናቱ ማብራሪያ ላይም እንደተብራራው የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ነበር። በዚህ ጥናት ውጤት ግን የተመጣጠነ በመሆኑ በሁለቱም ጾታዎች ያለው የተሳትፎ ምጥጥን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ቢደረግ።

# ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ንጋቱ፡፡ (1994)፡፡ *የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ትስስር አላቸውን?* በመጽሔት ትምህርት ቅጽ 6፣ ቁ. 13፡፡ አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ድ.፡፡

ለዘር አሊ፡፡ (2004)፡፡ "በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውንና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርትቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በላይ ሰይድ፡፡ (1992)፡፡ "የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ኤርምያስ ጥላሁን፡፡ (1996)፡፡ *በትምህርት ስኬታማነትን የሚያጎናጽፉ መርሆዎች፡፡* አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ፡፡

ግዛቸው አግማሴ፡፡ (2014)፡፡ "ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት (በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ጎርፍነሽ ታደሰ፡፡ (2011)፡፡ "አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የክፍል ተሳትፍ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ትንተና (በዲውሮ ዞን ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Ahmed, S. (2015). Education: Traditional Vs. Modern Perspective. *American Research Journal of English and Literature*, 1 (2), 1-4.

Allwright, D & kathleeni, M. B. (1991). *Focus on the Language Classsroom.* Cambridge: Cambridge Unviersity Press.

Amidon, E. J. (1976). The Role of the Teacher in the Classroom: A manual for understanding and improving teachers' classroom behavior. Association for Productive Teaching. New York.

Bailey, K. & Savage, L. (1994). *New Ways in Teaching Speaking, Teachers of English to Speakers of Other Languages.* Alexandria, VA.

Bonwell, C. C. and Eison, J. A. (1991). *Active Learning; Creating Excitement in the Classroom.* Washington: George Washington University Press.

Borich, D. G. (2004). *Effective Teaching methods.* 5th Edition. pearson Education Ltd.

Bronti B. (2018). *The Relationship Between the Big Five Personality Traits and Authentic Leadership*. Walden University.

Brown, H. D. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching*. (3th edition). New York: Longman, Inc

Byrne, D. (1987). *Techniques for Classroom Introdaction*. New York, Longman.

Candlin, N. C. & Mercer, N. (2000). *English Language Teaching In Its Social Context*. Routledsge: New Fetter Lane London.

Cochran, L. H. (1989). *Administrative Commitment to Teaching*. Cape Girardeau: Step Up, Inc.

Cohen, M. (1991). Making class participation a reality. *Political Science & Politics*, 24(4), 699-703.

Cruickshank, D. R. (1999). *The Act of Teaching*. Boston: M.C Graw-Hill Companies, INC.

Dhand, H. (2004). *Techniques of Teaching*. New Delhi, Ashisk Publishing House.

Doff, A. (1988). *teaching English Atraining course for teachers*. London: Cambridge university press.

Dornyei, Z. (2007). *Research Methods in Applied Linguistic*. Oxford: OPU.

Eggen, P. D, & Kauchak, D. P. (2013). *Educational Psychology: Windows on Classrooms*. (Ninth Edition). Peason Education, Inc.

Evertson, C. M., Anderson, C. W., Anderson, L. M., & Brophy, J. E. (1980). Relationships Between Classroom Behaviors and Student Outcomes in Junior High Mathematics and English Classes. American Educational Research Journal, 17(1), 43—60.

Farrant, J. S. (1980). *Principles and Practices of Education*. *(2nd ed)*. London: Longman Groups UK Ltd.

Fassinger, P. A. (1995). Professors' and students' perceptions of why students participate in class. *Teaching Sociology*, 24(1), 25-33.

Feldman, D. H. (1999). The development of creativity. In R.J. Sternberg (Ed.), *Handbook of Creativity* (pp. 169-186). New York: Cambridge University Press.

Hart, B., & Risley, T. R. (1995). *Meaningful differences in the everyday experience of young American children*. Paul H Brookes Publishing.

Hill, M, T. (2007). Class Room participation. U.S, Military Academy: West point.

Jacobs, G. (1988). Cooperative Goal stracture, Away to Improve Group.Activityes *INELT Journal*, 42(2), 97-101.

Jonsen, L. (2007). *The Student centered- class room*. cambrige; cambrige university press.

Kauchalk, P. D. (1993). Learning and Teaching. 2nd Edition. U.S.A. Library of congress cataloging in Publication data.

Marx, M. H. & Marion, E. B. (1977*). Fundamentals and applications of Learing*. Newyork: Macmillan pulishing Co. Inc.

Moore, K. (2001). *Class room Teaching skill*. New rork: Mc Graw hill companies.

Mortimore, E. A. (1988). *School Matters.* London, *Institute of Education*

Muijs, R. (2003). *Effective Teaching Evidence* and practice. London: Paul Chapmon publishing.

Nichols, R. C. (1978). Policy Implications of the IQ Controversy. *Review of Research in Education*, 6(1), 3-46.

Norris, H. G. (1972). *Analysis and modification of classroom Behavior.* New jersey: printice Hall, INC.

Nunan, D. (1988). *The Learner-Centered Curriculum: A study In Second Language teaching.* Cambridge; Cambridge university press.

Nunan, D. (1993). *Introducing Discourse Analysis*. London: Penguin English.

Petress, K. (2000). An Operational Definition of class participation. Retrieved December 23, 2022, From: http//www,vmpi'maine,edu/petreess/ArticleAOl.pdf

Reed, J. S. & Bergemann, V. E. (1995). *A Guide to Observation and Participation in the Classroom: An introduction to Education* (2nd edition). Asheville, NC: The Dushkin Publishing Group, Inc.

Rena, B. L. & Doorlag, D. H. (2011).*Teaching students with special needs in General Education Classrooms*. pearson Education Ltd.

Richards J. C. & Lockhert C. (1996). *Reflective Teaching in Second Langauge classroom*. 15th Edition. Cambridge: Cambridge University press.

Richards, J.C. (2001) Curriculum Development in Language Teaching. CUP, Cambridge.

Sensan, B. (1997). *How to Teach English*. Oxford: Oxford University Press.

Skinner, E. C. (1985). *Educational psychology*. (4th edition). Prentice Hall. Inc. Englewood Clifts. N.J.

Slavin, R. E. (2018). *Educational Psychology. Theory and Practice*. (10th Edition). pearson Education Ltd.

Smith, D. H. (1992). Encouraging students' participation in large classes: A modest proposal. *Teaching Sociology*, 20(1), 337_339.

Stevenson, J. S. & Joy, A. P (1994). *Learning principles, processes and practices.* Cassell Educational Limited.

Sunderland, J. (1992). Geender in EFL Class. ELT Jornal, 46 (1),81-90.

Thomas, A. (1987). *Looking in Class Rooms.* Newyork: *Harper and Row* Publishers.

Thomas, A. (1991). *Classroom Interaction*. Oxford: Oxford University Press.

Tony, W. (1987). Role of Teachers and Learners. Oxford: Oxford University Press.

Tudor, L. (1993). Teacher Roles in the Learner-Centered Classroom. *ELT Journal,* 47 (1), 22-31.

Weaver, R. R. & Qi, J. (2005). Classroom organization and participation: College students'Perceptions. *The Journal of Higher Education*, 76 (1), 570-601.

Zoltan, D. (2005). *The Psychology of the Language Learners Individual difference in Second Language Acquisition*. Noffingham: University of Noffingham.

## አባሪ 1፤ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ መጠይቅ

**በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ**

***ውድ ተማሪዎች፡-*** የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በክፍል ውስጥ ያለህን (ያለሽን) ተሳትፎ በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ መጠይቁ ያንተን (ያንቺን) የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚፈትሽ 22 የምርጫ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም አንተ(አንቺ) የምትሰጠው (የምትሰጭው) መልስ ይህንን ጥናት ውጤታማ ወይም ውጤት አልባ ሊያደርገው ስለሚችል ለቀረቡት እያንዳንዱ ጥያቄዎች በግልፅ እና በታማኝነት ምላሽ እንድትሰጠኝ (እንድትሰጭኝ) በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜህን (ጊዜሽን) ሰውተህ (ሰውተሽ) ይህን የፅሁፍ መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ በመሆንህ (በመሆንሽ) ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

***ማሳሰቢያ፡-*** ስም መፃፍ አያስፈልግም፤ በስም ምትክ መለያ ኮድህን (ኮድሽን) ሙላ (ሙይ)፡፡

- ከሌሎች ተማሪዎች በመኮረጅ መሙላት አይፈቀድም፡፡

መለያ ኮድ፡-______________

ጾታ፡-__________________

***መመሪያ፡-*** በቀጣይ ገጽ ባለው ሰንጠረዥ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚለኩ የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች የምትስማማበትን (የምትስማሚበትን) አማራጭ የስምምነት መልሶች ወክለው ከቀረቡት ከ1-5 ቁጥሮች አንዱን በመክበብ መልስ ስጥ (ስጪ)፡፡ በዝርዝር ጥያቄዎቹ የቀረቡ አማራጭ የመልስ መወሰኛ ቁጥሮች ውክልናቸው እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

5 በጣም እስማማለሁ

4 እስማማለሁ

3 በመጠኑ እስማማለሁ

2 አልስማማም

1 በጣም አልስማማም

“በጣም እስማማለሁ” ማለት ሁልጊዜ፣ “እስማማለሁ” ማለት አብዛኛውን ጊዜ፣ “በመጠኑ እስማማለሁ” ማለት በከፊል ከአንተ (ከአንቺ) ሀሳብ ወይም ተግባር ጋር ይስማማል ማለት ነው፡፡ በአንጻሩ “አልስማማም” ማለት አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም “በጣም አልስማማም” ማለት ደግሞ ሁልጊዜ ከአንተ (ከአንቺ) አስተሳሰብ ወይም ተግባር ጋር አይመሳሰልም ማለት ነው፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
| | **በጥያቄና በአስተያየት መልኩ የሚቀርብ** | | | | | |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ጥያቄ በሚጠይቁበት ወቅት ለጥያቄዎች ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2 | ያልገቡኝ ጥያቄዎች ሲሆኑ መምህሬን እጠይቃለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3 | መምህሩ ካልጠየቀኝ በስተቀር እጄን በማውጣት ምላሽ አልሰጥም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4 | መምህራችን ተግባራትን ሲሰሩ ወይም ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ ተሳስተዋል ብዬ ካሰብኩ አስተያየት እሰጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5 | ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ መምህራችን እንድንመልስላቸው ከጠየቁን ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | **በጥንድ ወይም በቡድን ውይይት** | | | | | |
| 6 | የቡድን ወይም የጥንድ ውይይት እንድናደርግ ስንታዘዝ በምንወያይበት ጉዳይ ሀሳብ እሰጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7 | በቡድን ወይም በጥንድ ውይይት ወቅት አስተማሪያችን ካላየኝ ሀሳብ አልሰጥም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8 | የቡድን ውይይት ተግባር በሚሰጠን ወቅት ማወያየት ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9 | የቡድን ውይይት ሲሰጥ ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 10 | የቡድን ውይይቱን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቼ (ጽብረቃ) አቀርባለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11 | የሌሎች ቡድን አባላት የቡድን ውይይቱን ሲያቀርቡ አስተያየት እሰጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | የክፍል ተግባራት ላይ ያለ ተሳትፎ | 7 | | | | |
| 12 | የአንብቦ መረዳት ተግባራት ሲሰጥ ተግባራቱን እሰራለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 13 | የመጻፍ ተግባራት ሲሰጡ በታዘዘው መልኩ እጽፋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 14 | በክፍል ውስጥ የሚሰጡ የመናገር ተግባራትን እሰራለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | የማዳመጥ ተግባራትን እሰራለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 16 | የስነጽሑፍና የሰዋሰው ተግባራት ሲሰጡ በታዘዝኩት መልኩ እሰራለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 17 | ውጤት (ነጥብ) የማይያዝበት ክርክር ወይም ውይይት ላይ እሳተፋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | ጽብረቃ (Presentation) ማቅረብ | 12 | | | | 16 |
| 18 | የተሰጠነው የግልም ይሁን የቡድን ስራ ጽብረቃ እንድናደርግ ስታዘዝ ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 19 | የግልም ስራ ሲሰጥ ጽብረቃ አቀርባለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 20 | የቡድን ስራ ሲሰጥ ቡድኑን በመወከል ጽብረቃ አቀርባለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 21 | በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ እንድናቀርብ እድል ሲሰጡን በማቅረብ እድሉን እጠቀምበታለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 22 | የተማርነውን ትምህርት እንድንከልስ (በገለጻ እንድናቀርብ) እድል ሲሰጥ አቀርባለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

## አባሪ 3፤ የጥያቄ ማውጫ ሰንጠረዥ

የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት — አጠቃላይ ውጤት - ፶

የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተና — ፈተናው የሚሰጠበት፡- ፳፻፲፰ ዓ.ም

ክፍል፡- ፱ኛ

| ምዕራፍ | ምንባብ | አበይትና ንዑሳን ርዕሶች | የጥያቄ ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ቋንቋና ህብረተሰብ | ● በምንባቡ የተካተቱ<br>☛ የቋንቋ ምንነት<br>☛ የቋንቋ አገልግሎት | 2 | |
| | | ● ማዳመጥ/መናገር<br>♦ በምክንያትና ውጤት የተገለጸ ሐሳብ | 1 | |
| | | ● መጻፍ<br>☛ በምክንያትና ውጤት የተገለጸ ሐሳብ | 1 | |
| ፪ | ስነ ቃል | ● በምንባቡ የተካተቱ<br>☛ የስነ ቃል ምንነት፣ ባህርያት፣ አይነቶች፣ ተግባራት | 3 | |
| | | ● መጻፍ<br>☛ የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ<br>☛ የግጥምና የዝርው የአነባበብ ስልት መመሪያ | 1 | |
| | | ● ማዳመጥ/መናገር<br>☛ በምክንያትና ውጤት የተገለጸ ሐሳብ | 1 | |
| | | ● ሰዋስው<br>☛ የምዕላድ ምንነት<br>☛ የምዕላድና የቃል አንድነትና ልዩነት<br>☛ የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች | 2 | |
| ፫ | ቤተ መጻህፍትና ስነ ጽሑፍ | ● በምንባቡ የተካተቱ<br>☛ የስነ ጽሑፍ ምንነት<br>☛ የስነ ጽሑፍ መኖር ምክንያቶች<br>☛ በተጻፈና ባልተጻፈ ስነ ጽሑፍ መካከል ያለው ልዩነትና አንድነት | 3 | |
| | | ● መጻፍ<br>☛ የአንቀጽ ምንነት፣ መዋቅር<br>☛ ተራኪ ድርሰት<br>☛ ስርዓተ ነጥብ /ነጠብጣብ እና ድርብ ሰረዝ /<br>☛ የጊዜ ቅደም ተከተል | 2 | |
| | | ● ማዳመጥ/መናገር<br>☛ የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ | 2 | |
| ፬ | ልቦለድ | ● ሥነ ጽሑፍ<br>☛ የልቦለድ ምንነት፣ አይነቶች፣ አላባውያን<br>☛ ዘይቤ /ተነጻጻሪ ፣ ሰውኛ እና ተለዋጭ/ | 3 | |
| | | ● ማዳመጥ/መናገር<br>☛ የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ | 1 | |
| | | ● ሰዋስው<br>☛ የቃል ክፍሎችን መለየት<br>☛ የሀረግ ምንነትና አይነቶች | 2 | |
| | | ● መጻፍ<br>☛ አያያዦችና መሸጋገሪያ ቃላት/ ሀረጋት<br>☛ አረፍተ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ<br>☛ የአስተዋጽዖ መንደፍ ጥቅም | 2 | |
| | | ● ስነ ጽሑፍ<br>☛ የግጥም ምንነት፣ ባህርያት፣አይነቶች | 3 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ስነ ግጥም | ☛ የግጥም ሙያዊ ቃላት<br>☛ የግጥምና የዝርው ልዩነት | | |
| | | ⬟ማዳመጥ/መናገር<br>☛ ጽሑፍን አጥንቶ በቃል ለማቅረብ የሚረዱ ነጥቦች | 1 | |
| | | ⬟ መጻፍ<br>☛ የግጥምን ሀሳብ ወደዝርው መቀየር | 1 | |
| | | ⬟ሰዋስው<br>☛ የአረፍተ ነገር ክፍሎች/ባለቤት ፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀፅ | 2 | |
| | አጠቃላይ ጥያቄ | ⬟ የግጥም እና የዝርው ምንባብ (አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች)<br>☛ ቀጥተኛ መረዳት<br>☛ አጠቃላይና ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት<br>☛ ማብራራትና መተርጎም<br>☛ መገምገም<br>☛ ዳራዊ መረዳት<br>☛ የቃላት ዐውዳዊ ፍቺ | 8 | |
| | | ⬟ ፈሊጣዊ አነጋገር | 1 | |
| | | ⬟ ምሳሌያዊ አነጋገር | 1 | |
| | | ⬟ የቃላት<br>🌢 ተመሳሳይ ፍቺ<br>🌢 አውዳዊ ፍቺ/ አገባባዊ ፍቺ<br>🌢 ተቃራኒ ፍቺ<br>🌢 እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 7 | |
| | | **አጠቃላይ የጥያቄ ብዛት** | **50** | |

## አባሪ 4፤ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

### በ2015 ዓ.ም በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

የተሰጠ ሰዓት፡- 1፡30

**ውድ ተማሪ፡--** የዚህ ፈተና ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለህን (ያለሽን) ክህሎት እና እውቀት በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ ፈተናው አራት ክፍሎች አሉት፡፡ በአራቱም ክፍሎች የተካተቱ ጥያቄዎች ብዛት 50 ሲሆን ሁሉም ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው የሚይዙት ነጥብ 1 ነው፡፡ በመሆኑም አንተ(አንቺ) የምትሰጠው (የምትሰጭው) መልስ ይህንን ጥናት ውጤታማ ወይም ውጤት አልባ ሊያደርገው ስለሚችል ለቀረቡት እያንዳንዱ ጥያቄዎች ያለህን (ያለሽን) እውቀትና ክህሎት በመጠቀም ምላሽ እንድትሰጠኝ (እንድትሰጭኝ) በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜህን (ጊዜሽን) ሰውተህ (ሰውተሽ) ይህን ፈተና ለመስራት ፈቃደኛ በመሆንህ (በመሆንሽ) ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

***ማሳሰቢያ፡–*** ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

- ከሌሎች ተማሪዎች በመኮረጅ መሙላት አይፈቀድም፡፡
- ጀምሩ ተብሎ እስኪነገር ድረስ የፈተናውን ጥያቄዎች ማንበብ አይፈቀድም፡፡

***መመሪያ ፩፡-*** ከተራ ቁጥር 1 እስከ 8 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ምንባቡን ባንክሮ በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጪ/ ምረጥ፡፡

ጋን በገል ይታጠናል ይባላል፡፡ ጋንና ገል በሸክላነታቸው አንድ ናቸው፡፡ አንድ ትንሽ ሸክላ አንድን ትልቅ ሸክላ የቃና ለውጥ እንዲያደርግ ማጠኛ ይሆናል፡፡ ከማህበረሰባዊ ግንኙነት አንፃር ሲታይ አንድ ግለሰብ አንድ ማህበረሰብ ከአንድ ዓይነት ይዞታና ሁኔታ ወደ ሌላ የተሻለ ይዞታና ሁኔታናእንዲለወጥ ምክንያት ወይም መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ ግለሰቡ የማህበረሰቡን ሥርዓትና መለያ ባህርያት በወጉ መገንዘብ አለበት፡፡ ግንዛቤው በከፊል ከማህበረሰቡ የወል ግንዛቤ፣ ባህርይና ተግባር ያፈነገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ እንደዚህ ያለ አፈንጋጭ ግንዛቤ የያዘ ግለሰብ፤ ይዋል ይደርናእንጂ ግንዛቤው ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ማዳረሱ አይቀርም፡፡ እንደዚህ ያለ ግለሰብ ለውጠኛ ማለትም፤ ለለወጥ የቆመ የለውጥ ሰልፈኛ ነው፡፡

ለውጠኝነት አፈንጋጭነት ስለሆነ በአጠቃላዩ ማህበረሰብና በአመራሩ የሚሞገስ ባህርይ አይደለም፡፡ ስለዚህም ምን ጊዜም በአመራሩ በኩል ርኩስ ሃሳብ እየተባለ ሊጥላላ ይችላል፡፡ ለውጠኛውም ርጉም እየተባለ ሊወገዝ ይችላል፡፡ መርገሚያውም ሆነ ማውገዣው ርግማን የምንለው የቋንቋ ዘርፍ ነው፡፡ በሚስለው አስፈሪ ምስልና በሚጭረው ኃይለኛ አሉታዊ ስሜት ከሌላው የቋንቋ ዘርፍ ይለያል፡፡ ዓላማው አፈንጋጭነትን ማዳከምና ነባሩን ሥርዓት ማበረታታትና እድሜውን ማራዘም ነው፡፡ "አመራሩ የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" ሲል፤ ለውጠኛው ቅቤ እንዲወጣው ወተቱ "ሊናጥ የግድ ነው" ባዩ ነው፡፡

አጠቃላዩ ህብረተሰብና አመራሩ የነበረውና ያለው እንደ ነበረና ኖእንዳለ ረግቶ እንዲቀጥል የሚፈልገውን ያህል ለውጠኛ ግለሰብ ከነበረውም ሆነ ካለው የተወሰነው እንዲንቀሳቀስና እንዲለወጥ የግል ግንዛቤ ያስገድደዋል፡፡ ይህ ሁኔታኖ ግለሰባዊ ግንዛቤ ከማህበራዊ ግንዛቤ፣ ባህርይና ተግባር ጋር በተቃርኖ እንዲቆም ያደርጋል፡፡ ይህ የተቃርኖ ግንኙነት ግለሰቡን ለማህበረሰባዊ ነቀፌታ ብሎም ርግማን ይዳርገዋል፡፡

ምንጭ፡- በፕሮፌሰር ባዬ ይማም የቀረበ ፅሑፍ (፳፻፭ ዓ.ም)
የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፣
መድበለ ጉባዔ

1. ፀሐፊው ለምንባቡ መንደርደሪያነት የተጠቀመው________________ ነው፡፡
   - ሀ. ፈሊጣዊ አነጋገርን
   - ለ. ምሳሌያዊ አነጋገርን
   - ሐ. የእንቆቅልሽ ጥያቄን
   - መ. ሰምና ወርቅን
2. "ገል" በምንባቡ ውስጥ የወከለው ምንድን ነው?
   - ሀ. አንድን ማህበረሰብ
   - ለ. የሸክላ ስባሪን
   - ሐ. የሸክላ ዕቃዎችን ሁሉ
   - መ. አንድን ግለሰብ
3. "ለውጠኛ" የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ የያዘው ፍቺ ____________________ ነው፡፡
   - ሀ. ለለውጥ የቆመ
   - ለ. ነውጠኛ
   - ሐ. የማህበረሰብ ስርዓት
   - መ. ተቃራኒ ሀሳብ የያዘ
4. በምንባቡ ውስጥ ለውጠኝነት እንዴት ተገልጿል?
   - ሀ. የማህበረሰቡን የወል ግንዛቤ አዳብሯል
   - ለ. በአመራሩ ተወድሷል
   - ሐ.በአፈንጋጭነት አስፈርጇል
   - መ.በማህበረሰቡ ተሞግሷል
5. ሥርዓቱ እንደነበርና እንዳለ እንዲቀጥል የሚፈልጉት__________________ ናቸው፡፡
   - ሀ. ነውጠኞች
   - ለ. ህብረተሰቡና አመራሩ
   - ሐ. ለለውጥ የተሰለፉት
   - መ. አፈንጋጮች
6. የምንባቡ መሠረታዊ መልዕክት ምንድን ነው?
   - ሀ. ነውጠኞች ለለውጥ ምክንያት እንደሚሆኑ
   - ለ. ማህበረሰብ ተደጋግፎ ቢኖር ውጤት ሊገኝ እንደሚችል
   - ሐ. የረጋ ወተት ቅቤ እንደሚወጣው
   - መ. አንድም ሰው ቢሆን ለለውጥ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል
7. ለውጠኛው በማህበረሰቡና በአመራሩ የተፈረጀው ከሚከተሉት በአንዱ አይደለም፡፡
   - ሀ. እንደ እርጉም ነው፡፡
   - ለ. ርኩስ እንደሆነ ተደርጎ ነው፡፡
   - ሐ. ተወግዞ ነው፡፡
   - መ. እየተሞገሰ ነው፡፡
8. በምንባቡ ውስጥ በ"ጋን" ተወክለሎ የቀረበው ምንድን ነው?
   - ሀ. ጠላ መጥመቂያ የሸክላ ዕቃን
   - ለ. አንድን ግለሰብ
   - ሐ. አንድን ማህበረሰብ
   - መ. የለውጥ ሥርዓትን

***መመሪያ ፪፡-*** ከተራ ቁጥር 9 እስከ 16 ዓረፍተ ነገሮች ይዘት በሚገባ በመረዳት ትክክል የሆኑትን ‹‹እውነት››፣ ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት መልሽ/ መልስ፡፡ [፩ ነጥብ]

9. የቃል ክፍሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍልነት የሚቀይረው ጥገኛ ምዕላድ የእርባታ ምዕላድ ነው፡፡

10..ማስታወሻ ስንይዝ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስፈር ተገቢ ነው፡፡

11.መስተዋድዶች ለተለያዩ ሰዋስዋዊ ባህርያት ቅርጻቸውን የማይለዋውጡ መካን ቃላት ናቸው፡፡

12.የቋንቋ ማህበራዊ ተግባር የተናጋሪውን ማንነት ማሳወቅ ነው፡፡

13.የእንስሳት መግባቢያ እንደሰው ልጅ ቋንቋ በስርዓት የተሰደሩ ድምፆች ስብስብ ሳይሆን ኢደመነፍሳዊ ነው፡፡

14.በአንድ ዓ.ነገር ውስጥ አንድ ግስ ብቻ ካለ ግሱ ማሰሪያ አንቀፅ በመባል ይታወቃል፡፡

15.ስነቃል በጽሑፍ ያልሰፈረ ነገር ግን በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦችን የሚያጠና ስለሆነ የስነ ጽሑፍ ዘርፍ ሊሆን አይችልም፡፡

16.ክርክር በሚከናወንበት ጊዜ የተከራካሪ ወገን ሀሳብን ማክበር ተገቢ ነው፡፡

**መመሪያ ፫፡- ከተራ ቁጥር 17 እስከ 22 ያሉ በምድብ ‹‹ሀ›› ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በምድብ ‹‹ለ›› ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምድ/ አዛምጂ፡፡**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 17.ሸረከተ | ሀ. ቀጭን |
| 18.ተደራሲ | ለ. ማገድ |
| 19.መግታት | ሐ. አጭር |
| 20.ቋንጣ | መ.ቁልቅለት |
| 21.ጉቶ | ሠ. አቀበት |
| 22.ዳገት | ረ. ገረደፈ |
| | ሰ. ታዳሚ |

**መመሪያ ፬፡- ከተራ ቁጥር 23 እስከ 50 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በአጠያየቁ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ፡፡ [፩ ነጥብ]**

23.ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣

አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና፡፡ የዚህ ግጥም ምጣኔ

ሀ. የወል ቤት ሐ. ሰንኀ መገን

ለ. ድብልቅ መ. ቡሄ በሉ

24. ‹‹ከችግር ጋር ሲታገል የኖረ ሰው ቆዳው ይወፍራል_____ጅማቱ ይጠነክራል የተጣለበት ሸክም መሸከም ይችላል፡፡›› በክፍት ቦታዎች መግባት ያለበት ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ‹‹ ›› ሐ. ፤

ለ. ፣ መ. ፡፡

25.በውይይት ዝግጅት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. ንግግራችንን መልክ ማስያዝ ሐ. ርዕሱን ማስተዋወቅ

ለ. የርዕሱን ጥልቀት መወሰን መ. መረጃ መሰብሰብ

26. አስቴር፡- ______________________________________

መርየም፡- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚነበብ ስላልመሰለኝ አላነበብኩም ነበር፡፡

አስቴር፡- በይ ከዚህ በኋላ ጥሩ ውጤት ለማግኘት ጠንክረሽ አንብቢ፡፡

የአስቴርና የመርየምን ምልልስ በማጤን በክፍት ቦታው ሊቀርብ የሚችለውን ሀሳብ ____________ ነው፡፡

